# ራእይ፡ ምዕራፍ አምስት ክፍል I

በጣም እናመሰግናለን፡ ወንድም ኔቪል፡ ጌታ ይባርክህ፡ ወንድሜ።

2 እንደምን አደራችሁ፡ ወዳጆች። ዛሬ ጠዋት፡ እንደገና ወደ ተበርናክል መመለስ መቻላችን፡ እና ይህ ሰዓት፡ በጌታ ቃል ዙርያ ሆነን፡ ለማለዳው አምልኮ እና ለፌሎሺፕ አንድ ላይ መሆናችን መታደል ወይም ልዩ ዕድል ነው እለዋለሁ። ያኔ ድሮ "'ወደ ጌታ ቤት እንሂድ፡' ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ፡" የሚል እንደተነገረ አምናለሁ። ይህም በድጋሚ፡ ከወንድም ኔቪል እና ከሌሎች ጥሩ ውድ ወዳጆቼ ጋር ለመሆን ነው።

3 ይመስለኛል ከኋላ በኩል ቀዝቃዛ፡ ወይም ሙቀት እንደሆነ አምናለሁ። እና **እዚያ** ጋር ይመስለኛል፡ ምናልባት፡ በእጆቻችሁ ልትጠቀሙባቸው የምትችሉ የእጅ ማራገቢያዎች አሉን። እ—እ... የሚያንቀሳቅሳቸው ሞተር ካገኛችሁ፡ ማቀዝቀዣዎች አሉን። እንደውም፡ ወደዚህ አካባቢ በብዛት አሉ፡ አሁንም ያሉ ይመስለኛል። አንዳንዶች የዝማሬ መጻሕፍት እና ሌላ-ነገሮች ሲጠቀሙ ይታዩኛል። እንዲህ ነው... አገልግሎት የምናደርግባቸው አንደኛው ነገር፡ ወደፊት ሞቃት የሆኑትን ስፍራዎች—እንተዋቸዋለን። ስለዚህ... ዛሬ እዚህ የተገኘንበት ምክንያትም፡ እነዚያን ስፍራዎች ለመተው ነው። ይህን ማድረግ የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ያም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው።

4 እናም የቤተ ክርስቲያኒቱን መልካም ዘገባ እንዴት እየተሻሻለ እንዳለ መስማቴ፡ ከጌታ ጋር መሄዳችሁና፡ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ስጦታዎች እንዴት እንደሚሰራባችሁ በመስማቴ፡ በጣም ደስ ብሎኛል። እስኪጠቀምባችሁ ድረስ በትክክለኛው እና በጠባቡ መንገድ መሀል እንደሚጠብቃችሁ በመተማመን፡ ወደ ቀኝ እና ወደ ግራ ሳይላወስ ስለሚጸና ትሁት እና ቅን ልባችሁ፡ እግዚአብሔርን በእውነት አመሰግናለሁ።

5 ቀደም ሲል እዚህ ወጥተው ያን ግሩም ዝማሬ የዘመሩት፡ ይመስለኛል፡ **በሰማይ እንባ የለም**፡ ብለው የዘመሩት ወንድም ኮልቪን እና ሴት ልጁ ማመስገን እፈላግለሁ። እጅግ ያምራል። በእውነት ተባርኬበታለሁ።

6 ወንድም ኔቪል ስለኔ እና ስለሱ ከአመታት በፊት እንደተናገረው፡ እኔም ስለ ወንድም ኮልቪን፡ ሁለታችንም ከብዙ ዓመታት በፊት እንተዋወቃለን ማለት እችላለሁ። እና እነዚያን የጥንት የወንጌል ዝማሬዎችን ሲዘምር በመስማቴ ልጆቹም በጌታ መንገድ ሲያሳድግ በማየቴ፡ ልቤን የሚያሞቅ ነገር ነው። እግዚአብሔር አሁንም እሱን የሚወዱ እና እሱን የሚንከባከቡ ሰዎች እንዳሉት ሳውቅ ደስ ይለኛል። ስለዚህም እናመሰግነዋለን።

7 አሁን፡ ከተመለስኩ በኋላ፡ ብዙዎች በእምነት እንደተጠመቁ ሰምቻለሁ፡ በዚህም ምክንያት በጣም ደስተኞች ነን። ጥሩ ጓደኛዬ ወንድም ኤልመር ጋበሃርት፡ ማዶ ላይ ይታየኛል። ወደ እምነት የተጠመቀው ገና አሁን መሆኑን ተረድቻለሁ፡ ስለዚህም በእውነት አመሰግናለሁ። ያም ድሮ አደን አብረን ስናድን የነበርን ከኬንታኪ የሆንን ጓዶች መዘጋጀታችን ያሳያል፡ ገደቡን እንጠቀምበታለን፡ አይደለም እንዴ?

8 ትዝ ይለኛል (ሮድኒ ተመልሶ ከገባ፡ ከኋላ ካለው ክፍል ሆኖ እንደሚሰማኝ አውቃለሁ፡ ቻርሊም ከፊቴ ተቀምጧል።) ወደዚያ ስንሄድ ትዝ ይለኛል። “እንግዲህ፡ ሽኮኮ ስለሆነ፡” ሁሉም ይወዱታል፡ እናገኛለን ብለው በማሰብ አልፈው ይሄዳሉ። እኔም ልክ አይደላችሁም ብዬ እመክራቸው ነበር። አሁን ግን ሁሉም... ቡድናችን በሙሉ ኢየሱስን አምነው ተቀይሯል ስለዚህ ወደ ቀጣዩ ቀበሌ ወርደን በዚያ የሚገኙትም እንዲታረሙ ማድረግ ይኖርብናል። መልካም ነገር ነው።

9 ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ዞር ብዬ አያለሁ፡ እንደ ማንኛውም አገልጋይ፡ የተጓዝኩትን ጉዞ ዞር ብዬ አየዋለሁ፡ እና ስለ ሁሉም ነገሮች—አሰባለሁ፡ ዘሩን ዘርቼ ይሆን—እላለሁ።

10 ከእናንተ... ብዙዎቻችሁ... አሜሪካዊው ጆኒ አፕልሲድን በደንብ ታውቁታላችሁ። ሌላም፡ በሰዊድን አገር ውስጥ—አበባን በመዝራት፡ እንደሱ የሚታወቅ ሌላ ሰው ነበረ። እና አሁን በሰዊድን ውስጥ ብዙ የሚያማምሩ አበቦች ያሏቸው በዚህ ምክንያት ነው ይላሉ፡ የአበቦች ዘር ይዘሩ ነበርና፡ ዘሮቹ የሚበቅሉበትን አነስተኛ መሬት ካገኘ ያድጉለታል። አበቦችን ይወድ ስለነበር በየመንገዱ ዘሩን በተነ። አሁን እሱ የለም አበቦቹ ግን ህያዋን ናቸው።

መለያየትን ከኋላችንን ትተን
የእግር አሻራዎች በጊዜ አሸዋ ላይ፥

የእግር አሻራዎች፡ ወይም ሌላ፡
በህይወት ጉዞ ላይ እየቀዘፍን ሳለን፡
መርከብ ተሰብሮበት ተሰፋው እልቆ የነበረ ወንድም፡
አይተነው፡ ልባችን እንደገና ይታደሣል።

11 ሁላችንም ማየት የምንወደው ያ ነው፡ ከዚህ በፊት ያደረግነው ሌሎችም እንዲጠቀሙበት—ያስቻልነው ነገር ማየት እንፈልጋለን።

12 ከጥቂት ቀናት በፊት በዚህ ከተማ ውስጥ፡ ከአንድ ታማኝ ወዳጄ፡ ከሜዲካል ዶክተር፡ ከሳም አዴር ጋር ቁጭ ብዬ እያወራሁ ነበር። እርሱም፡ “እንዴት ነህ፡ ቢል? ”

13 እኔም፡ “ኦህ፡ በጎ ነኝ፡ እላለሁ፡ ዶክ።” “አንተስ? ” አልኩት፥

14 እርሱም፡ “ኦህ፡ ታማሚው በዛ።” “ዛሬ ከሰአት በኋላ አስራ አምስት ምርመራዎች ነበሩብኝ፡” አለኝ።

15 እኔም፡ “አይ፡ ችግር ካልተገኘባቸው ምርመራ’ኮ መልካም ነገር ነው።” እንዲህ አልኩት፡ “ታውቃለህ፡ ያኔ... ” እንዲህ እንዲያ እያልን ስለ ህጻንነታችን ተጫወትን። እና “ይኸውልህ፡ ዶክ፡ ምን ያህል ጊዜ በህይወት እንደምቆይ አላውቅም። ሁለታችንም በአምሳዎቹ ላይ ነን፡” አልኩት።

እርሱም “እውነት ነው፡ ቢል፡” አለኝ።

16 እና እንዲህ አልኩት፡ “በእነዚህ ዓመታት፡ በሰላሳ-አንድ የአገልግሎት ዓመታት ውስጥ ግን፡ እርሱ የሚመጣባትን ሰዓት እየተጠባበቅኩ ልቤን አዘጋጅቼ ቆይቻለሁ። ስለዚህ ቢመጣም አልፈራም።”

እርሱም “እውነት ነው፡” አለ።

"እኔ በጣም የሚያስደስተኝ ነገር ለሌሎች መኖር ነው፡" አልኩት።

17 እርሱም፡ "ህይወትን ህይወት የሚያደርገው፡ እውነተኛ ነገር ያ ነው፡ ማለት... ለራስህ በምታደርገው እና በሰራኸው ነገር ሳይሆን፡ ለሌሎች በምታደርገው ነገር ነው" አለኝ።

18 አያችሁ፡ በእውነት የምትኖሩት ያኔ ነው። ስለዚህ በመካከላችን ይህን ያላደረገ ለሌላ ሰው ለመኖር ያልሞከረ ሰው ካለ፡ እስኪ ለሌላ ሰው መኖር ሞክር፡ እስኪ ሞክረው፡ ከህይወት በምታገኛቸው ነገሮች ለራስህ ሳትሆን ለሌሎች እየሆንክ ስትኖር ህይወት የያዘችልህን ነገር ምን እንደሆነ ተመልከት። ከምታስቡት ሁሉ በላይ... ከሃብት እና ከየትኛውም ነገር በላይ የተባረከ ነገር ሆኖ ታገኙታላችሁ። የሌሎች ሰዎች የህይወት ሸክም ላይ አንዳች ነገር ማድረግ መቻል... ማለት፡ ህይወት በራሱ'ኮ ሸክም ነው። እና ሌሎች ቀለል እንዲልላቸው ማድረግ ነው። ካልሞከራችሁት በቀር ለሌላ ሰው አንዳች ነገር ማድረግ፡ ምን ያህል ደስታ እንዳለው አታውቁትም።

19 እና ይህ ነገር በጌታ አገልግሎት ያሳለፍኳቸው ሰላሣ-አንድ አመታት (በቅርብ ይሞላል) እንዳስብ አደረገኝ። እና ሰው ሁሉ ወደ መጨረሻ የአገልግሎት ሰዓቱ ሲቃረብ ወይም የፍጻሜ ሰዓቱ ስትደርስ ይህን ነገር የሚያስብ ይመስለኛል፡ እና ወደ ኋላው ዞሮ የሰራቸውን እና ያሳካቸውን ነገሮች ይፈትሻል፡ እና ዋናው ነገር ለሌሎች መኖርህ ነው እንዳልኳችሁ፡ "ያደረግከው ነገር አለ? " እንግዲያውስ... እንደተናገርኳችሁ፡ የተደረገ ነገር ካለ ፈትሹ።

20 ወደ መንገዴ ፍጻሜ ስደርስ እንዴት ይሆን ይሆን ብዬ ብዙ ጊዜ እገረማለሁ፡ ማናችንም ብንሆን የትኛው ሰዓት እንደሚሆን፡ አናውቀውምና። ስለዚህ በሕይወቴ ውስጥ ያለፍኩበትን ዱካ ወደ ኋላ ለመመልከት እያሰብኩ ነበር እና ልዩ ልዩ ኮረብቶችንና ቋጥኞች ዓለቶችንና ከባባድ ቦታዎችን እንዲሁም ለሰላሳ ሩጫዎችንም፡ በእነዚያ ጊዜያቶች ያደረግኳቸውን ሁሉ አየሁ። ከዕለታት አንድ ቀን መሄጃዬ በደረሰ ጊዜ ሁሉ በግልጽ ይታያል። በሁላችንም እንዲሁ ይሆናል። ጊዜው ሲደርስ፡ ለእያንዳንዳችን የተገለጠ እንደሚሆን—ሁላችንም እርግጠኞች ነን።

21 ይህም ከመናገር ይልቅ ብሮጥ ወደሚሻለኝ ንግግር እንድናገር ይመራኛል ወይም ይገፋፋኛል። አንድ ነገር እንድናገር ያስገድደናል... ይህን መናገሬ የልቤን ውስጥ ያደማኛል፡ ይሁን እንጂ የምናገረው ነገር እንድናገር እገደዳለሁ፡ ይህም እየተቀዳ እና ወደፊት ዓለም እንደሚሰማው አውቃለሁ፡ ይሁን እንጂ—በአንድ ምክንያት ከአገልግሎቴ እንድለይ ተገድጃለሁ በመለየቴም እጅግ አዝናለሁ። ምናልባትም ብዙዎቻችሁ ሰምታችኋል፡ ቢሮዬን፡ እና ሌላውን ዘግቼ፡ መስኩን ትቼዋለሁ።

22 ጌታችን ወዴት እንደሚመራኝ አላውቅም፡ እና እርሱ እንዳደርግ በሚፈልገኝ ነገሮች ላይ፡ እኔ የመግዛት ስልጣን የለኝም። ይሁን እንጂ ስለማይቀርልኝ የመንገዴ ፍጻሜ እያሰብኩ ነው። እናም በህይወት ጉዞዬ እጅግ የማዝንባቸው ብዙ ስህተቶችን ሰርቻለሁ፡ ሰው መሆኔ፡ እና በድካም እና በመሳሰሉት ምክንያት፡ ይመስለኛል፡ ይህም መፈጸም የማንፈልጋቸው ወይም መናገር የማንፈልጋቸው ነገሮች... አረ ማድረግ የማንፈልጋቸውን እንድናደርግ

ያደርጋልና። ነገር ግን የሰው ልጅ ድክመት መሆኑ፡ ታዲያስ፡ እነዚያ ጊዜዎች——ይኖሩናል። ይሁን እንጂ...

23 ልቤ ውስጥ ማድረግ የሚሰማኝ አለ ከተባለ፡ በጉዞ መጨረሻ ላይ እነዚያን የጌታችንን የኢየሱስን ቃላት፡ እንዲህ ሲል መስማት ነው፡- “መልካምና ታማኝ ባሪያዬ፡ መልካም ሰርተሃል።” “ወደ እኔ ና” ብሎ ሲናገር፡ በዚያ ብገኝ ብዬ ምኞቴን ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ፥ ነገር ግን “መልካም ሰርተሃል፡” ሲለኝ መስማት እናፍቃለሁ። በመጀመሪያ፡ ያኔ ድሮ መጽሐፍ ቅዱስ በሚጻፍበት ዘመን፡ “ወደ እኔ ና፡” የሚለውን፡ ድምጽ አልሰማሁም፥ “መልካም ሰርተሃል፡” ሲለኝ መስማት ግን እናፍቃለሁ።

24 እናም ሁል ጊዜ መሆን የምፈልገው ነገር፡ እና መሆን የምፈልገው የልቤ ምኞት፡ ለጌታዬና ለመድኃኒቴ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ እውነተኛ አገልጋይ መሆን ነበር። ምስክርነቴ ንጹህ፡ አጭርና-ግልጽ፡ የጸናሁ፡ በስሕተቶቼ ሁሉ በልቤ ሁሉ እርሱን የሚወድ መሆን እሻለሁ። ይህንንም ዛሬ ጠዋት በሙሉ ልቤ አደርገዋለሁ።

25 እናም፡ በዚያ ምክንያት ግን፡ አገልግሎቱን እተዋለሁ እንድል ያስገድደኛል፡ እንዲህ እንድል የሚያስገድደኝ ነገር በሕዝቡ መካከል የተነሣ ነገር ስላለ ነው፡ ይህም፡ “አገልጋይ” ወይም “ወንድም” ተብዬ ከምጠራበት ማዕቀፍ ውጪ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ሊሉኝ የዳዳቸው ስላሉ ነው፡ ሌላም ይሉኛል... ይህም እኔን ጸረ ክርስቶስ ያሰሆነኛል። እናም ከእርሱ ለመውሰድ በእርሱ ፊት የክርስቶስ ተቃዋሚ ሆኜ ከመገኘቴ በፊት በእግዚአብሔር ፊት ተሰፋ እንደቆረጠ ሆኜ እቀርባለሁ።

26 ከጥቂት አመታት በፊት ስ——ስምቼዋለሁ እና ቀልድ መሰሎኝ ነበር። እና ሁለት ወንድሞች አገኘሁና (ዛሬ ጠዋት በሰብሰባው ላይ አንዳቸውንም አላየሁም)፡ ከመካከላቸውም ሁለቱ ሶስቱ አንድ ጊዜ አሳ በማጥመድ ጉዞ ሳለን፡ እንዲህ በሚል ርዕሰ ወደ እኔ ቀርበው ተናገሩኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አንተ የተቀባው መሲህ፡ ክርስቶስ አይደለህምን? ”

27 እጆቼንም በሁለቱም ወንድሞች አንገት ላይ፡ ወይም፡ በሁሉም ላይ አደረግሁና፡ እንዲህ አልኳቸው፡ “ወንድሞች፡ እኔ የክርስቶስ እውነተኛ አገልጋይ ለመሆን ምንም ብሞክር እንኳ፡ እንደዚያ ያለ ነገር እንድትናገሩ አልወድም። እና ስለ እኔ እንዲህ አይነቱ ነገር ከተባለ፡ በንፁህ ህሊናዬ መስኩን እለቃለሁ፡ እናንተም ያንን የምታደርጉ በዚያን ጊዜ ላድናቸው ለነበረ ነፍሳት ሁሉ ተጠያቂ ትሆናላችሁ፥ እያችሁ፡ ከመስክ እንድወጣ በማድረጋችሁ።” እና ያን ጊዜ የከሰመ መሰሎኝ ነበር።

28 ከዚያም ጥቂት ተጨማሪ ጊዜ ሰማሁ። ነገር ግን አልከሰመም። እና በቀደምለት በካናዳ አንድ ወንድም በኪሱ ውስጥ የታሸገ ትንንሽ ትኬት ነገር አሳየኝ፡ “ዊልያም ብራንሃም ጌታችን ነው” ይላል፡ በዊልያም ብራንሃም ስም እናጠምቃለን። እና ትንሽ... ወዳጄ በመሆኑ... አለ የተባለ ጠላት፡ ጠላቴ ቢሆን ኖሮ ቀልድ መሆኑን አውቅ ነበር። ነገር ግን የተወደደ፡ ውድ ወንድማችን ኃጢአቱን እና ሰንፍናውን ሊናዘዝ መጣ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመሆኔ በእኔ ስለማመኑ ተናገረኝ።

29 እና እኔ ቤት ውስጥ ደብዳቤዎች አሉ፡ እና ከቺካጎ እና ከተለያዩ ቦታዎች ጥሪዎች ይደርሱኛል፡ ያንን ዶግማ ታምናለህ ወይ ብለው ይጠይቁኛል።

30 እና ባለፉት ጥቂት ቀናት ውስጥ የመጡ ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች ተቀብያለሁ፡ እና ከተለያዩ ቦታዎች ጥሪዎች ደርሰውኛል፡ ስለእኔ፡ ክርስቶስ ስለመሆኔ ይናገራሉ። ወንድሞች ሆይ፡ ይህ አስፈሪ፡ አሳፋሪ፡ ፈሪሃ እግዚአብሔር የራቀው የዲያብሎስ ውሸት ነው! አያችሁ? ተመልከቱ፡ እኔ ወንድማችሁ ነኝ። ስለዚህ፡ ይህ ማንኛውንም አገልጋይ መስኩን ያስለቅቀዋል። ይህም ክርስቶስን የሚወድ ሁሉ ከነገሩ እንዲሸሽ ያደርገዋል።

31 በቅርብ ጊዜ የዛሬ አመት አካባቢ፡ መጀመሪያ በሰማሁት ጊዜ፡ በጌታ ፊት ቀርቤ ነበር። ከዚያም ወደ ጌታ ሄድኩና ዮሐንስ እየሰበከ በነበረ ጊዜ የሚገልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጠቅሶ አሳየኝ፡ እንዲህ እስኪሉ ድረስ... ሁሉም በልባቸው እስኪገረሙ ድረስ፡ በምድር ላይ ለብዙ አመታት ነቢይ እንዳልነበራቸው፡ ምናልባት ዮሐንስ መሲህ ሊሆን ይችላል ይሉ እንደነበር። ስለዚህ እኔ... ዮሀንስ፡ ወደ እርሱ ቀርበው ጠየቁት፡ እርሱም እንዳልሆነ ነገራቸው። በሉቃስ ምዕራፍ 3 ላይ፡ ከቁጥር 15 ላይ አንብቡት። እና ስለዚህ... ነገር ግን እንዲህ አይነቱ እንዲረጋጋ አደረገው፡ እኔም በዚያው ጸጥ እንዲል ተውኩት።

32 ወደዚህ ጉዳይ ስንመጣ ግን፡ አንድ ነገር መደረግ እንዳለበት ተረዳሁ። እኔም ይህን እላለሁ፡ "በወንዙ አጠገብ የታየው የእግዚአብሔር ራእይና መልአክ፡" (ይህ ነገር ለቤተ ክርስቲያን፡ ወይም ለዓለም የመጨረሻ መልእክቴ ወይም የመጨረሻው ነገር ከሆነ) "ስለ እግዚአብሔር መልአክ ካላችሁ፡ የተነገሩ ነገሮች በሙሉ እውነት ናቸው።"

33 እናም ሰዎች ብዙ ጊዜ ነብይ ብለው ሲጠሩኝ ዝም እላለሁ፡ በእንግሊዘኛ አባባል **ነቢይ** ማለት "ሰባኪ፡ ትንቢት ተናጋሪ፡ የቃሉ ትንቢት ተናጋሪ፡" ወዘተ ማለት ነው። ያ ከሆነ ዝም እላለሁ ምክንያቱ እንዲያ አይነት ነገሮች ንቃችሁ ማለፍ ትችላላችሁ፥ "የተቀባው ክርስቶስ" ወደ መባል፡ ወይም እንዲህ አይነቱ ነገር፡ ከመጣ ግን ከአቅሜ በላይ ነው። ይህን ዝም ብዬ አላልፈውም።

34 እና ከዚያ በኋላ... መጣሁ... በካናዳ የነበረን ስብሰባ ለቀን ከወጣን በኋላ፡ ነገሩ በአስኪሞዎቹ ወይም በህንዶች መካከል እንደተሰማ ተረዳሁ፡ በመካከላቸው ገብቶ ነበርና።

35 እና ነገሩ ውስጤን እጅግ አቆሰለኝ። እና አደን ለማደን ቀደም ብለን ያስያዝነው ቀጠሮ፡ እንድሰርዝ ተገደድኩ። የአደን አደጋ ፈራሁ፡ ምን ማለቴ እንደሆነ ከገባችሁ። አሁን እዚህ ከቆምኩት በባሰ መልኩ፡ እጅግ ተንቀጠቀጥኩ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ዝም ማለት አይሆንልኝም፡ የሠላሳ-አንድ አመታት አገልግሎት በሙሉ ወደ ዲያቢሎስ ቱቦዎች ሲገባ ዝም አልልም፡ ማለት... እኔ በሄድኩ ጊዜስ፡ ምን ይሉ ይሆን? "ይኸው እርሱ ነው፡ በትክክል እርሱ እንዲህ ነበር"፡ በህዝቡ ላይ ያሳደርኩት ያን ሁሉ ተጽዕኖ፡ ምን ውስጥ እንደሚገባ ተመልከቱ፡ የክርስቶስ ተቃዋሚ እንድሆን ያደርገኛል። ስለዚህ ይህን ችላ ማለት አልችልም!

36 እንዲህ ከመባል፡ "ጠመንጃው አባርቆበት ወደቀ፡ ተብዬ ብሞት ይሻለኛል፡ ብዬ አሰብኩ... " ከዚያም ሊሆን የሚችለው ታየኝ... ገና ስላላደገው፡ስለ

ትንሹ ልጄ ዮሴፍ፡ ወዘተ አስብኩ። እና ለማደን ምንም ፍላጎት ስላልነበረኝ፡ ጫካውን ትቼ ወደ ቤት መጣሁ።

37 ከሰምንት እስከ አስር ቀናት ድረስ እጅግ አቆሰለኝ፡ እንደውም አእምሮዬ የሳትኩ—እስኪመስለኝ ሆንኩ። እና ሁሉም ሰው ከእኔ እንዲርቁ እና ብቻዬን እንዲተዉኝ ጠየቅኳቸው ምክንያቱ እጅግ በተበሳጨ እና በተጨነቀ መንፈስ ስለነበርኩ ነው።

38 እኔም ገረመኝ፥ ከጠላቴ ቢሆን ኖሮ፡ ምንም ችግር አልነበረውም፡ ስቁበት አልፈው ነበር፥ ከውድ ወንድሞቼ፡ ከውድ እህቶቼ መካከል በመሆኑ ግን፡ እጅግ ጎዳኝ። እኔም አልኩት፡ "ጌታ ሆይ፡ ነገሩ... ነገሩ ለእኔ በጣም ጥሩ ነው፡ እንዲሁ ወጥቼ በአንተ እጅ እተወዋለሁ። ሌላ—ምንም ማድረግ አልችልም።"

39 ከጥቂት ምሽቶች በፊት፡ እርግጠኛ ለመሆን፡ ከጌታ ዘንድ—ተጎበኘሁ። እና ከወዳጆቼ መካከል አንዳንዶች፡ ቢጫ እና ጥቁር የሆነ እባብ—እሹሩሩ ሲሉ አየሁ፡ እና ውዲያው፡ እየነገረኝ ሳለ፡ እነሆ፡ ነገርዬው እግሬን ነደፈኝ። ነገር ግን ደሙ ብርቱ ከመሆኑ የተነሣ በእኔ ላይ አቅም አልነበረውም። እና ወደ ታች ተመለከትኩኝ፡ እና ከዚያ በፊትም በተመሳሳይ ቦታ ተነድፌ ነበር። እናም ጠመንጃዬ አቀባብዬ በፍጥነት ዞርኩና ተኩሼ—ነገሩን ተኮስኩበት፡ እና ነገሩን መኃሉ ላይ መታው።

40 አንድ ወንድምም እንዲህ አለ... ተኩሼ ጭንቅላቱን ለመምታት ስዞር፡ እንዲህ አለ፡ "ተው እንደዛ አታድርግ፡ አጠገብህ የወደቀውን ዱላ አንሳ።" እና ዱላውን ለማንሳት ጀርባዬን ሳዞር፡ ወደ ትንሽ የውሃ ውስጥ፡ ወዳቆረው ውኃ ውስጥ ተምዘግዝጎ ገባ።

41 እንዲህ አልኩ፡ "ከእንግዲህ፡ ይህ ወንድም (ወንድሞች ሁሉ) ይህን ስለተገነዘቡ ጉዳት አያደርስም ስለዚህ መጨረሻው ይህ ነው።" "ስለቆሰለ... ለሞት በሚያደርሰው ቁሰል ስለተመታ፡ ይሞታል፡" አልኩኝ።

42 ስለዚህ እኔና ወንድም ኔቪል ባለንባት፡ በዚህ ቤተ ክርስቲያን መጥታችሁ ተመሳሳይ ጥያቄ ያቀረባችሁልኝ፡ ብዙዎቻችሁ የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ይህን ጥያቄ አቀርብላችኋለሁ፥ ወንድሞች፡ እህቶች ሆይ፡ በእናንተ ፊት የክርስቶስ እውነተኛ አገልጋይ ለመሆን አልተጋሁምን? ወንድማችሁ ለመሆን አልተጋሁምን? አሁንም፡ በማንም ይሁን፡ በተወደዱ ሰዎች ውስጥ የገባ መናፍስት ነው። ብዙ ሰዎች ተመሳሳይ ጥያቄ ጠይቀውኛል። ይሁን እንጂ—መናፍስት ነው፡ ስለዚህ ዛሬ በከባድ ቆሰሎ ይመታ ዘንድ ተሰፋ አደርጋለሁ እኔም ወደ አገልግሎቴ በፍጥነት እንድመለስ በፍጥነት ይሙት። እስከዚያ ድረስ፡ እያንዳንዳችሁ፡ እንድትጸልዩልኝ እጠይቃችኋለሁ። ምን እንደማደርግ አላውቅም። ሰፍራዬ ለድርድር ቀርቧል። ችላ ማለት አልችልም፡ አ—አ—አልርቅም፡ እጅግ ያሰከፋኛል። ስለዚህም... ጸልዩልኝ እላችኋለሁ።

43 በተጨማሪም፡ ይህን አሰቡ፡ እኔን የክርስቶስ ባርያ እንደሆንኩ ካመናችሁኝ፡ አምናችሁኝ ከሆነ፡ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**! ይህን አሰቡ፡ "ያ ስሕተት ነው! ከውሸት ነው!" "ስህተት ነው! ከእሱ ጋር ምንም ግንኙነት አይኑራችሁ!" እኔ ወንድማችሁ ነኝ።

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ፥

44 የሰማይ አባት ሆይ፡ ሥጋዬ እየተንቀጠቀጠ ነው፡ እጆቼም ተጨባብጠዋል፡ ጣቶቼም በጫማዬ ውስጥ ተጨናንቀዋል። አምላኬ ሆይ፡ ምሕረት አድርግ። ጌታ ሆይ፡ ለዚህ የሚገባኝ፡ ምን አደረግሁ? ጌታ ሆይ፡ ለእኔ እና ለሁሉም፡ ትራራ ዘንድ እለምንሃለሁ። ጌታ ሆይ፡ በዚያ ያሉት፡ የተወደዱ ሰዎችም፡ ስሕተታቸውን አይተው ያደረጉትን ነገር እንዲያውቁ አግዛቸው፡ የወንድማቸውን ልብ ሰብረዋልና... የወንድማቸው ብቻም አይደለም፡ ነገር ግን የአዳኛችን፡ የሰማይ አባታችንም ጭምር እንጂ። ጌታ ሆይ፡ ሰህተታችንን ይቅር እንድትለን እጸልያለሁ። የክርሰቶስ ቅዱስ ደም አሁን ሰውነታችንን ያስተሳሰር፡ ጌታ ሆይ፡ ልባችንን በክርስቲያናዊ ፍቅር እና ኅብረት ያስተሳሰረ ማሰሪያም የተባረከ ይሁን።

45 እግዚአብሔር ሆይ፡ ወንድሞቻችንን እና እህቶቻችንን የተጠጋውን ጠላት... ከዚህ በኋላ ሊኖር በማይችልበት ገዳይ ቁስል ይቁሰል፥ በቃ ይሙት፡ ጌታ ሆይ። አባት ሆይ፡ አንተ ያንን ስታደርግልን፡ እኔም ወደ መስክ እመለሳለሁ። እስከዚያ ቀን ድረስ ግን፡ ጌታ ሆይ፡ እነሆ ልቡ ተሰብሮ፡ የሚጠብቅ፡ የሚጠብቅ ባርያህ ነኝ። ማድረግ ከምችለው ነገር ሁሉ በላይ ነው። በእንባ እና በለቅሶ እየተማጸንኩ፡ እጅግ በኃይል ሞክሬአለሁ፡ ጌታ ሆይ (ልቤን ታውቃለህ።) ያን ያህል ርቀት ከመድረሱ በፊት ለማሰቆም ጥሬአለሁ፡ አሁን ግን ምንም ማድረግ ከምችለው በላይ አልፏል። ሰለዚህ፡ አባት ሆይ፡ ከዚህ መድረክ ተነሰቼ ለእነዚህ ሁሉ ዓመታት የሰበክኩበት በእጆችህ አደራ ሰጥቼአለሁ። በእጅህ አሳልፌ አደራ እሰጥሃለሁ።

46 አሁንም፡ በገዛ መለኮታዊ መንገድህ፡ አባት ሆይ፡ አንተ ተመልከተው። እና ሁሉም ነገር ካለቀ እና ሁሉም ነገር ካለፈ በኋላ፡ ባሪያህ ይመለሳል። እስከዚያ ድረስ ከአንተ ለመሰማት እጠባበቃለሁ፡ ጌታ ሆይ።

47 አሁንም ባርከን ዛሬም ታላቅ አገልግሎት አድርግልን፥ እኛ እዚህ ያለነው፡ ለዚህ ብቻ ሳይሆን፡ በአጠቃላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ፡ ግልጽ ለማድረግ ነው። አባት ሆይ፡ እኔ አንተን እንደምወድህ እምኜህም ለአንተ እንደቆምኩ፡ ያውቁ ዘንድ ነው፡ መሻቴም—ይህ ነው፡ መሄድ ካለብኝም፡ ጌታ ሆይ፡ እኔ አንተን ባመንኩበት እና በተማመንኩበት በንጹሕ ምሰክርነት፡ ልሂድ። ፍቃድህ ይሁን። እነሆም አመሰግንሃለሁ በሚመጡ ዘመናት ሁሉ ላይ በኢየሱስ ክርሰቶስ በኩል ክብር እሰጥሃለሁ። አሜን።

48 አሁን፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ ከመጽሐፍ ቅዱሰ... ዛሬ ጠዋት ጥሩ ነገር ይሆናል ብዬ አሰባለሁ፡ ወንድም ኔቪሌ ቅር ካላለው፡ ለጥቂት ደቂቃዎች በዚያ ጉዳይ ላይ እንቀጥላለን...

49 ሰለዚህ፡ ከእንግዲህ... በማናችሁም ዘንድ ይህ ሲወራ እንዳልሰማው። ጸልያችሁ አሰወግዱት፡ ዝጉት። አያችሁ? እንዲህ አይደለሁም... እ—እኔ— የኃምሣ-ሁለት ዓመት ሰው ነኝ፡ ምናልባት እንደኔ አሳብ፡ እግዚአብሔር ከራራልኝ፡ የቀረኝ ትንሽ ህይወት ነው፡ እያንዳንዷ የሕይወቴ ጊዜ ሰለክርሰቶስ ብኖራት ብዬ እመኛለሁ። ሰለዚህ፡ ትቼ የምወጣው ሰለተገፋሁ መሆኔን፡ አትርሱ።

50 አሁን፡ በራእይ መጽሐፍ፡ በጥናት ላይ ሳለን በቀደም ባቆምንበት ምዕራፍ 4 ላይ... ራዕይ፡ ምዕራፍ 4 ላይ፡ ይመሰለኛል፡ በምዕራፉ ቁጥር፡ የመጨረሻ

ክፍል ላይ። እሺ፡ ራዕይን የምትወዱት ሰንቶች ናችሁ? በጣም ጥሩ! አሁን፡ እንደሚመስለኝ በ 5ኛው—በ 5ኛው ምዕራፍ ላይ ያቆምን ይመስለኛል፡ አይደል? 4ኛውን ምዕራፍ ላይ፡ ስለ አራቱ ሕያዋን ፍጥረታት ላይ፡ ደርሰናል። አሁን፡ እነዚያን ያለፉትን ነገሮች እየረሳን፡ ወደ ቃሉ እንቅረብ።

51 እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ እየተጨነቅን ቢሆንም እርዳን፡ ወደ ቃሉ እንቀርባለን። ያለፈውን እየረሳን፡ አሁን ከፍ ወዳለው ጥሪ ምልክት እንዘረጋለን። የክርስቶስ አገልጋይ ለመባል የሚያደርስ ከፍ ያለውን ጥሪ። ዛሬ ጠዋት ቃሉን ሰጠን የተራበን ነፍሳችንን መግብ፡ ጌታ ሆይ፡ ያንን ውድ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በመጠባበቅ፡ እንገኛለንና። ጌታ ሆይ፡ ሀጢያታችንን እና በደላችንን ይቅር በለን እና፡ ባሪያዎችህ እንድንሆን አቤቱ በመካከላችን ተገኝ። በኢየሱስ ሰም እንጠይቃለን። አሜን።

52 አሁን፡ የቤተ ክርስቲያንን ዘመናት፡ የመጨረሻዎቹን ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት አይተናል። ስለዚህም፡ አሁን፡ አንዳንዶች እየሰሩት ይገኛሉ... የቤተ ክርስቲያን ዘመናትን፡ እየጻፉት ይገኛሉ። ከዚያም **ወደ ማን መገለጥ** ወደ ራዕይ መጽሐፍ ምዕራፍ 4 ላይ ገባን... የማን ነው? **የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ።** በላቲንኛ ቋንቋ፡ **መገለጥ** ማለት፡ **አፖካሊፕስ** ይሉታል፡ ትርጉሙም "ሊገለጥ ያለው፡ ሽፋኑን—ማስወገድ፡ እንዲታይ፡ እንዲከፈት ማለት ነው፡" የነበረው፡ ያለውና፡ የሚመጣው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ የዳዊት ሥርና ዘር እንዲታይ ማድረግ ማለት ነው።

53 አሁን፡ በ4ኛው ምዕራፍ፡ ዮሐንስ የቤተ ክርስቲያንን ዘመናት ካየ በኋላ ወደ ሰማይ እንደተወሰደ አይተናል። አሁን ትንሽ ዳራውን ለማየት ያክል እንየው፡ ከዚያም እንቀጥላለን...

54 ምናልባት የ 5ኛውን ምዕራፍ ጥቂት ጥቅሶችን ማንበብ ጥሩ ሊሆን ይችላል፡ ከዚያ በኋላ እንጀምራለን።

> **በዙፋኑ** ላይም **በተቀመጠው በቀኝ እጁ ላይ በውስጥና በኋላ፡ የተጻፈበት... በሰባትም ማኅተም የተዘጋ መጽሐፍን አየሁ።**
>
> **ብርቱም መልአክም መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ፡ ማኅተሞቹንም ይፈታ ዘንድ የሚገባው ማን ነው? ብሎ በታላቅ ድምፅ ሲያውጅ አየሁ፡**
>
> **በሰማይም ቢሆን፡ በምድርም ላይ ቢሆን፡ ከምድርም በታች ቢሆን፡ መጽሐፉን ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው፡ ማንም አልተቻለውም።**
>
> **መጽሐፉን ሊዘረጋ፡ ወይም... ሊመለከተው የሚገባው ማንም ስላልተገኘ እጅግ... አለቀስሁ።**
>
> **ከሽማግሌዎቹም** አንዱ፡ **አታልቅስ፥ እነሆ፡ ከይሁዳ ነገድ... የሆነው አንበሳ፡ እርሱም የዳዊት ሥር፡ መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ፡ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል** ነሥቶአል **አለኝ።**
>
> **አየሁም፡ እና፡ እነሆ፡ በዙፋኑና፡ በአራቱ እንስሶች መካከልም... በሽማግሌዎችም መካከል፡ እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፡ ሰባትም**

**ቀንደችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት፡ እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።**

**መጥቶም በዙፋን ላይ ከተቀመጠ ከዚያ ከቀኝ እጁ መጽሐፉን ወሰደው።**

የመጀመሪያዎቹ ሰባት ቁጥሮች ናቸው።

55 አሁን፡ አሁን፡ በራዕይ ምዕራፍ 3 ላይ፡ የቤተ ክርስቲያን ዘመን መጨረሻውን እናገኘዋለን፡ ፍጻሜውም ለብ ባለው፡ በሎዶቅያ የቤተ ክርስቲያን ዘመን ነበር። ከዚያ በኋላም፡ ወዲያው ዮሐንስ በመንፈስ ተነጥቆ፡ ወደ ሰማያትም እንደተወሰደ፡ እናያለን። እርሱም ያለውንና፡ የሚመጣውን፡ እና የነበረውንም አየ። ከዚያም፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ እስከ 19ኛው ምዕራፍ ድረስ እንደማትታይ፡ ተምረናል፡ ከዚያ በኋላ በደሙ ታጥባ፡ ከጌታዋ ጋር ትመለሳለች።

56 አሁን፡ በዚህ አንቀጽ መጨረሻ፡ ዮሃንስ አሁን ያለበት ሰፍራ ዳራውን ለመስራት ያህል፡ በመጨረሻው መልእክት ላይ አይተነዋል... ትናንት በተናገርኩባቸው አንዳንድ አውዶች ውስጥ፡ ባጭሩ እየተመለከትኩት ነበር። ስለዚህ ዮሃንስ ወደ ሰማይ ተወሰዶ እነዚያን ነገሮች አይቷል። እናም በዚያ ውስጥ እርሱ መገለጥ እንደሰጠኝ እስተውያለሁ፡ ይህም... እንደምታውቁት፡ ከትንሣኤውም በኋላ ብዙዎች ከእርሱ ጋር ነበሩ፡ አንዳንዶችም እንዲህ አሉ፡ “ይህ ደረትህን ተደግፎ የተቀመጠውን ሰው (ዮሃንስ) ወደፊት ዕጣፈንታው ምን ይሆናል? ”

57 ኢየሱስም ዘወር ብሎ እንዲህ አለ፡ “እስክመጣ ድረስ ቢቆይ ለአንተ ምን አግዶሃል? ” ስለዚህ እሱ...

58 ከዚያም አንድ ዶክትሪን ወጣ። ምን ያህል በቀላሉ እንደሚጀመር ተመልከቱ? በዚያም አንድ ዶክትሪን ወጣ ያም—ያም “ዮሐንስ የኢየሱስን መምጣት እስኪያይ ድረስ፡ ወይም እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ አይሞትም የሚል ነበር።” መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህም ዶክትሪን ወጥቷል ይላል።

59 ይሁን እንጂ፡ ኢየሱስ እንደዚያ በፍጹም አላለም። እርሱ ያለው፡ “እኔ እስክመጣ ድረስ ቢቆይ ምን አግዶሃል? ”

60 ስለዚህ፡ እርሱ ወደ ሰማይ መወሰዱን እና እዚያ እንዳለ ሆኖ ሁሉም ነገር ሲፈጸም እንደተመለከተ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ጌታ መምጣት ድረስ እንዳየ ተረድተናል። ዮሐንስ ራሱ በሕይወት አልኖረም... ዘጠና-እና ከዚያ በላይ ዓመት ሆኖት ኖረ፡ ከዚያም ወደ ፍጥሞ ከተሰደደበት ከተመለሰ በኋላ በተፈጥሮአዊ—ሞት ሞተ (ከሐዋርያት መካከል ብቸኛው እርሱ ነው)።

61 አሁን፡ የያዝኩት አንድ አሰደናቂ ነጥብ አለ... (ጥቁር ሰሌዳውን... አውርደውብኛል መሰለኝ፡ ይሁን እንጂ... ) ይህን አስፈላጊ ነገር ከመምታታችን በፊት ትንሽ አፅንዖት መስጠት እፈልጋለሁ። ኦህ፡ ይህ የከበረ ነገር ነው! ድንቅ፡ ድንቅ ምዕራፍ ነው።

62 ከዚያም ቀጣዩ ምዕራፍ እነዚህን ማኅተሞች በመክፈት ይጀምራል። ኦህ፡ ማይ! እናም ከዚያ ተነስተን በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ወደተለያዩ ቦታዎች መዳሰስ እንችላለን፡ ይህም እነዚህ ማኅተሞች ሲከፈቱ ምስጢራቸው ምን እንደሆን ለመዳሰስ ነው። ኦህ፡ በመንፈሳዊ ቪታሚኖች የበለፀጉ፡ የከበሩ ናቸው!

63 አሁን፡ ትኩረትዎን እንዲሰቡ ከምፈልጋቸው አስደናቂ ነገሮች ውስጥ አንዱን አይተናል፡ ይህም ዮሃንስ የቃልኪዳኑን ታቦት ባየ ጊዜ የተመለከተው (የ 4ተኛው ምዕራፍ መጨረሻው ክፍል) ስለ ህያዋን ፍጡራን የሚመለከት ነው። እስራኤል በጉዞአቸው ላይ ሳሉ አሰፋፈራቸውን እንዴት እንደነበረ ትዝ ይላችኋል? በመካከላቸው ይህ ነበር፡ አሁን፡ በዚያ፡ የህያው ፍጡር ፊት ነበር። እናም እነዚህ ፍጥረታት መላእክት እንዳልሆኑ፡ ሰዎችም እንዳልሆኑ አይተናል። ኪሩቤሎች እንደነበሩ አይተናል። በብሉይ ኪዳንም ከታቦት ጋር አይተናቸዋል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እናገኛቸዋለን። እንደገናም በጌታ ምጽአት ውስጥ፡ ኪሩቤሎች የምሕረት ወንበር ሲጠብቁ አይተናቸዋል።

64 ይህም የሰርየት መክደኛው ለሚቀርበው ግለሰብ በግሉ የተደረገለት ሰርየት ያለው ካልሆነ በቀር ማንም ወደዚያ መጠጋት አይችልም፡ ብቸኛው ወደ መቅደሱ መግቢያ... በደሙ ከተረጨ ብቻ ነው፡ ያን ጊዜ የምሕረት ወንበር ይሆናል። ደሙ ከተወሰደ በኋላ ግን፡ የፍርድ ወንበር ይሆናል።

65 እና፡ ኦህ፡ ማይ፡ የእግዚአብሔርን ፍርድ ሊቋቋመው የሚችል የለም። የምንፈልገው ምህረት ብቻ እንጂ፡ ፍርድ ሳይሆን፡ ጽድቅ-... ጽድቅ። ፍርዱ ፊት መቅረብ አንችልም፥ ምክንያቱ፡ ፍርዱ የሚጠብቀው፡ ቃሉን ብቻ ስለሆነ፥ ቃሉን መጠበቅም፡ “ከእርሱ በበላህ ቀን፡ በዚያ ቀን ትሞታለህ።” ፍርዱን ማን ይፈልጋል? ፍርዱን አልፈልግም። ምሕትረትን እሻለሁ። ኧረ፡ የእግዚአብሄር ምሕረት... የምሕረቱ ወንበር የተረጨ ይሁንልኝ!

66 ነገር ግን መቅደሱ የሚነጻበት ጊዜም ነበረ፡ ይህም የሚሆነው ደሙ ከምሕረቱ ወንበር በተነሣ ጊዜ የፍርድ ወንበር ሲሆን ጊዜ ነው።

67 አሁን፡ **አሁን** ወደዚያ ጊዜ እየተቃረብን ነው። አሁን በዚህ ዘመን፡ የመቅደሱ መንጻት፡ እና በምድር ላይ የሚመጣውን ፍርድ የሚሆንበት ጊዜ በመጠባበቅ ላይ ነን። አያችሁ? ደሙ እስካለ ድረስ፡ እግዚአብሔር ምድርን ሊያጠፋ አይችልም፥ ደሙ እስካለ ድረስ፡ ማንም በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኛ አይደለም። ሁሉም ሰው ትክክል ነው፡ ምክንያቱም ለሁሉም ሰው ማስተሰረያ አለ። ነገር ግን ማስተሰሪያውን አልቀበልም ብላችሁ በፊቱ ከቀረባችሁ ግን፡ ያን ጊዜ ኃጢአተኛ ናችሁ፡ ከምሕረቱ ውጪ ናችሁ። ስለዚህ ራሳችሁን ፈርዳችኋል። ይህ ግን ምሕረቱ እስካለ ድረስ ነው... የመቅደሱ መንጻት ሲመጣ ግን፡ ደሙ ከምሕረት ወንበሩ ይነሣል ከዚያም የእግዚአብሔር ቁጣ በምድር ላይ ይወርዳል። ኦህ፡ ማይ! ወይኔ! በዚያ ቀን ከእግዚአብሔር ምሕረት ርቀን እንዳንገኝ፡ እግዚአብሔር ይጠብቀን።

68 አሁን፡ በዚያ እንዳየነው... እዚህ ላይ መንፈሳዊ ለማስመሰል እሞክረዋለሁ፡ ወይም በእጄ እስልላችኋለሁ፡ እስራኤል አሰፋፈራቸው አራት ማዕዘኖች እንደነበሩ ልሳልላችሁ። ታቦቱን መኃል ላይ—ያስቀምጡታል፡ ከዚያ በኋላ በድንኳኑ በአራቱ ወገን ሦስት የእስራኤል ነገዶች ይሰፍራሉ፡ ሦስት ጊዜ አራትም አስራ ሁለት ነው፡ ወይም አራት ጊዜ ሦስት፡ ማለት፡ አስራ ሁለት ነው። ለሦስቱም ራስ ነበራቸው። የየነገዶቹም ራስም እንዲሁ...

69 ከመካከላቸው አንዱ ሮቤል ነበር፡ ሰፈሩም ሁልጊዜ—ወደ ደቡብ ነበር። እሱም የሰው ራስ ነበር። ኤፍሬምም በምዕራብ ነበረ፡ ሦስት ነገዶችም ነበሩት፡ እርሱም—በሬው ነበር። ከ... ከዚያም በምስራቅ በኩል ይሁዳ ነበረ፡ እርሱም

እንበሳ ነው። በሰሜንም በኩልም ዳን ነበረ፡ እርሱም ንስር ነበረ። አሁን፡ ልብ በሉ። ታስታውሷቸዋላችሁ? እንዴት በሰዕል እንዳስቀመጥናቸው፡ ሁላችሁም ትዝ ይላችኋል፥ ንስር፡ እና በሬ፡ እና—ሰው፡ እና እንበሳ።

70 አሁን፡ ልብ በሉ፡ ይሁዳ የምሥራቁን በር ይጠብቃል። ክርስቶስም "የይሁዳ ነገድ አንበሳ" ነው። እነሆ ከሰማያት በምስራቅ ይወርዳል፡ በበሩም መንገድ ይገባል። ከይሁዳ ነገድ ከምሥራቁ በር መጣ። እርሱም "የይሁዳ ነገድ አንበሳ" ነው።

71 እናም ዛሬ ማለዳ በሚመጣው መልእክታችን ላይ፡ እንረዳዋለን፡ አሁንም "የይሁዳ ነገድ አንበሳ፡ የዳዊት ጅማሬ፡ እና ሥር" መሆኑን እናውቃለውን። ዳዊት፡ የዘላለም ንጉሥ ነበር። ክርስቶስም በዳዊት ዙፋን ላይ፡ በሺህ አመት መንግስት የዘላለም ንጉስ ነው። "ዳዊትን የሚሽር አይኖርም።" ሃሌ ሉያ! "ዳዊትን የሚሽር አይኖርም!" እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል፡ ቃል ገባለት፡ "ዳዊትን ሊሽር የሚችል፡ አንድም የለም።"

72 እናንተም እንዲህ ትላላችሁ፡ "ዛሬስ፡ የአይሁድ ፈራጆች ወዴት አሉ? "

73 አሁንም ዘር አለው፡ ክርስቶስ በሥጋ ልጁ ነው። እነሆ በዚያ ተቀማጭ አለ። "ዳዊት ፈጽሞ አይወድቅም።" በትክክል። ክርስቶስም ዳዊት ከበቀለበት ሥር የወጣ "የይሁዳ ነገድ አንበሳ ነው።"

74 አሁን፡ የምህረት ወንበር ጠባቂዎች እንደነበሩ ለማወቅ ችለናል። የምህረት ወንበሩን ጠባቂዎች ናቸው። አልፎ መግባት የሚችል የለም፡ ወደ ምሕረት ወንበር ከመምጣቱ በፊት ነገዶቹን ቆርጦ ማለፍ ይጠበቅበታል። ምንም ነገር እነርሱን አልፎ፡ ወደ ምሕረት ወንበር ከመግባቱ በፊት ነፍሱን ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ በሰፈሩ ውስጥ ያለው እስራኤላዊ ሁሉ ይሞታል። ስለዚህ አሁን ያ የብሉይ ኪዳን ሥርዓት እንደነበረ ተረድተናል።

75 የአዲስ ኪዳን ሥርዓትም ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡ ይህም የምሕረት ወንበሩ፡ ተባቂዎች እንዳሉት ነው። ኦህ፡ እንደምትረዱት ተስፋ አደርጋለሁ! የምሕረት ወንበሩ አሁንም ይጠበቃል፡ ዛሬም ጠባቂዎች አሉት። እነዚያ ጠባቂዎችም ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስና፡ ዮሐንስ፡ የሐዋርያት ሥራን መጽሐፍ የሚጠብቁ መሆናቸውን አውቀናል፡ እርሱም በሐዋርያት መካከል የተደረገው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፡ እርሱም—የአዲስ ኪዳን አዲሱ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ነው። አራቱም የወንጌል ጸሐፊዎች፡ ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስና፡ ዮሐንስ፡ ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ራሱ፡ እግዚአብሔር መሆኑን ለማሳየት ሁሉም የሰርየት ወንበሩን ይጠብቃሉ። እያንዳንዱ መጽሐፍ፡ ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስ፡ እና ዮሐንስ፡ እያንዳንዳቸው የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛ ወንጌል እና የመንፈስ ቅዱስን ተግባር ደጋፊዎች ናቸው።

76 አሁን፡ ከዚያ ውጪ ካላፍን ልክ አይደለም። እውነተኛውን መልእክት ግን ይደግፋል! በሐዋርያት ሥራ 2:38 ላይ እንደምናገኘው፡ "ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡" የሚሉትን ይደግፋሉ።

77 ዛሬ ግን "አባት፡ ልጅ፡ እና መንፈስ ቅዱስ" በማለት የሚጠመቁበትን ሌላ ስም አለማምደዋል። ይህን የሚደግፍ ቃል የለም! ዳራም የለውም። የለም—ያንን የሚጋርድ ምንም ነገር የለም፡ አንዳች የለም! እናንተም "ማቴዎስ ላይ

ተናግሯል፡” ትላላችሁ። ማቴዎስ ይደግፈዋል። ማቴዎስ 28... 1፡18 እንዲህ ይላል፦

> **... የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እንዲህ ነበር፡ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች... ጊዜ፡** ሳይገናኙ፡ **ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች።**
>
> ይህ ሁሉ የተደረገው... **ባሏ ዮሴፍ፡** (ይልቁንስ) **ጻድቅ ሆኖ፡... ሊገልጣት** ስላል**ወደደ፡** በዚህ መልኩ፡ በሰውር **ሊ—ሊተዋት አሰበ።**
>
> **እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፡ እነሆ፡ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፡ እንዲም አለው፡ የዳዊት ልጅ፡ ዮሴፍ ሆይ፡ እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ከእርሰዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና።**

78 ስለዚህ፡ መንፈስ ቅዱስ እና አብ የተባለው እግዚአብሔር አንድ አካል ናቸው ካልሆነ ግን ሁለት አባቶች ነበሩት ማለት ነዋ። አያችሁ? ስለዚህ ተመልከቱት!

> ልጅም **ትወልዳለች፡... ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ፡...**
>
> ... ይህም **በነብያት፡ እንዲህ የተባለው... ይፈጸም ዘንድ... ይህ ሁሉ ሆኖአል፡...**

79 እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሆናል፡ ስሙም አማኑኤል ይባላል፡ እርሱም እግዚአብሔር፡ አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በተባለው ስህተቶች እንዳይገቡ በሮችን በሚጠብቀው በአንዱ ስም ውስጥ ናቸው።

80 ከጥቂት ቀናት በፊት በቺካጎ፡ ከቺካጎ የአገልጋዮች ማህበር በፊት፡ ታላቂቱ ቺካጎ... ትዝ ይለኛል... መንፈስ ቅዱስ ማታ ላይ “በመስኮቱ አጠገብ ቁም፡” ብሎ ተናገረኝ። “የሆኑ አገልጋዮች ተሰብሰበው ቁርስ ላይ ሊጠሩህ ተማክረዋል፡” አለኝ። “በዚህ ጉዳይ ላይ ሊያጠቁህ ስለሆነ፡ ተጠንቀቅ፡” አለኝ።

81 እኔም “አመሰግንሃለሁ፡ ጌታ ሆይ፡” አልኩት። የሚዘጋጅበት ስፍራም አሳየኝ።

82 እኔም ሄጄ ለአንዳንድ አገልጋዮች፡ ለወንድም ካርልሰን እና ለወንድም ቶሚ ሂክስ፡ እንዴት እንደሚሆን ነገርኳቸው። “እናንተ ያዘዛችሁት ስፍራ፡ በዚያ አይሆንም። በሌላ ስፍራ እንገናኛለን፡” አልኳቸው። ዶክተር ሜድ እንዴት እንደሚቀመጥ፥ አንድ ጥቁር ሰው እንዴት እንደሚገባ፡ **በዚህ** አቅጣጫ እንደሚቀመጥ፥ ሁሉንም በዝርዝር ነገርኳቸው።

83 ያን ጊዜ በማለዳ፡ እንዲህ ተባባሉ... ልጄ እንዲህ አለኝ፡ “ዳዲ፡ ወደዚያ ንትርክ ልትሄድ ነውን፡” ብሎ ጠየቀኝ?

84 እኔም አልኩት “ለመነታረክ ወደዚያ አልሄድም። በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቼ፡ ወደዚያ እሄዳለሁ፡ እሱ እስካለ ድረስም፡ ያንን የምህረት መክደኛ ከሚጠብቀው ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እሄዳለሁ።”

85 እና በዚያም በተገናኘን ጊዜ፡ አንዳች ጥያቄ ለመጠየቅ እድል ሳያገኙ፡ መንፈስ ቅዱስ ተናገረኝ፡ "የምትናገርበት ጊዜው አሁን ነው፡" አለኝ።

86 እኔም "እዚህ ለምን እንደተሰበሰባችሁ አውቄአለሁ፡" አልኳቸው። እንዲህ አልኩ፡ "አሁን፡ ወንድም ሂክስ፡ አንተም ወንድም ካርልሰን፡ የክርስቲያን ቢዝነስ ሜን ዋና ኃላፊ፡" እንዲህ አልኳቸው፡ "ይህ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ከትናንትና ወዲያ እንደተናገረኝ በትክክል እየተፈጸ አይደለምን? ያንን አዳራሽ እንደማታገኙት፡ በዚህ ቦታ እንደምንሆ አልነገርኳችሁምን? " ያን ቀን ማለዳ ተረዱት። እኔም "አሁን ተመልከቱ፡ እያንዳንዱ ሰው በዚህ ይቀመጣ ተብሎ እንደተነገራችሁ እነሆ ተቀምጠዋል፡" አልኳቸው። "ልትጠይቁኝ የፈለጋችሁት ጥያቄ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጥምቀት በሚመለከት ነው፡" ብዬ ነገርኳቸው።

87 እንዲህ ሲሆን ሳለ... መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል እያነሣ እንዲህ መግለጥ እና መተርጎም ጀመረ፡ እነዚያም ሁሉ የሥላሴ አገልጋዮች በዚያ ተቀምጠው ነበር፡ እጆቻቸውን ከጠረጴዛው ስር እያሻገሩ እርስ በርሳቸው ሲጨባበጡና እንባም በጉንጮቻቸው ሲወርድ ነበር። ከመካከላቸውም ሰባ-ሁለቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠምቃቸው ዘንድ ተከትለውን ወደዚህ ተበርናክል መጥተዋል።

88 የስርየት ወንበሩ የተጠበቀ ነው፡ አያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ የስርየት ወንበሩን ጠባቂ ነው። በትክክል ሳይዛነፍ ማስቀመጥ አለብን... የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይሁን... በዚያ ተቀምጠው ያሉ ታላላቅ መልእክተኞች፡ ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስ፡ እና ዮሐንስ፡ የአዲስ ኪዳንን እያንዳንዱን ተግባር የሚደግፉ ናቸው።

89 አሁንም—አሁን፡ በዛሬው ማለዳ የመጀመሪያው የመልእክቱ ክፍለ ጊዜ የተናገርኩት ይህ ነው፡ እዚያው በወንጌል እንደተጠበቀ እናቆየው። አያችሁ? አይታችኋል? ወንጌሉ በጠበቀበት መልኩ እንዲሁ እንዲጠበቅ አድርጉት።

90 አሁን፡ በዚያ ዘመን እንደተረዳነው፡ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን የምሕረት ወንበር ይጠብቁት ነበር፥ በዚያም፡ ማቴዎስ፡ ማርቆስ፡ ሉቃስ፡ እና ዮሀንስ፡ ሁሉም ናቸው። የይሁዳም ነገድ አንበሳ ሳይቀር የምሕረት ወንበሩን ይጠብቅ ዘንድ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ፡ በገዛ ደሙ እንዲረጭ አደረገ። ዛሬም በዚህ ማለዳ፡ ታላቁ ድል ነሺ፡ እነሆ ቆሟል እርሱም አንድ ቀን ከምሥራቅ ይወርዳል እኛም እናየዋለን።

91 አሁን፡ በፍጥነት እንዘጋለን፡ የጥምቀት አገልግሎት እንዳለ አውቄአለሁ። ይህ ባለ ሰባት-ማሕተም መጽሐፍ ምንድን ነው? ኦህ፡ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር ነው! እዚህ ምን እንደሚል አስተውላችኋል፡ "በመጽሐፉ **ጀርባ** ላይ ሰባት ማኅተሞች እንደነበሩት"? ልዩ ነገር ነው... ኦህ፡ እግዚአብሔር አሁኑኑ ይርዳን ድፍረትንም ይስጠን፡ ፈጥቼም ቢሆን ዘግይቼ ወደ እናንተ ማምጣቴ አይቀርም። ተመልከቱ፡ ይህ በቃሉ ውስጥ የታጸፈ አይደለም፡ በቃሉ ጀርባ ላይ የታተመ ነው። መጽሐፉም በሰባት ማኅተሞች ታትሟል። የመጽሐፉ ምሥጢር ሁሉ በእነዚህ ሰባት ማኅተሞች የታተመ ነው። ይህ በመላው የራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ታላላቅ ምዕራፎች አንዱ ነው። ተመልከቱት፡-

**በዙፋኑም ላይ በተቀመጠው በቀኝ እጁ በውስጥና... የተጻፈ መጽሐፍ አየሁ ከውስጥ የተጻፈበት** (ውስጡ የተጻፈበት፡ ዛሬ ማለዳ የምናነበው ይህ ነው።) **እና... ከጀርባው፡ በሰባት ማሕተም የታተመ ነው።**

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን የማይናገረው፡ እዚህ ውስጥ በሰባት ማኅተሞች ታትሟል፡ የእግዚአብሔር ምሥጢር።

92 አሁን፡ ምንድን ነው? አሁን፡ ልብ በሉ። ማኅተም ማለት የተጠናቀቀውን ምርት ተምሣሌት ነው፡ ተፈትሾ ያለፈ ነገር፡ የተረጋገጠ፡ እና ከዚያም የታተመ ነው። ይህም... አሁን እኛም በመንፈስ ቅዱስ በመታተም የመዳናችን ቀብድ ይዘናል። የደኅነታችን ቀብድ ያ ነው።

93 አንድ ደቂቃ ወደ ኋላ እንመለስ። እ—እዚህ ጋር ጽፌ የያዝኩት ቃል አለኝ፡ ብዙ ስለሆኑ፡ ሁሉንም ለማየት ጊዜ... አይኖረንም። ግን ለአፍታ ያህል፡ ወደ ኤፌሶን እንመለስና፡ ከኤፌሶን 1ኛው ምዕራፍ... እናንብብ፡ ትክክለኛውን ትርጉምም ታገኙታላችሁ።

**በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ፡ ጳውሎስ፡ በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን፡...**

94 እናም፡ ዮሐንስም፡ ይህ መልእክት ለኤፌሶን ሰዎች፡ ለኤፌሶን እና በክርስቶስ ላሉት ምእመናን በማለት ጽፎላቸዋል፡ ጳውሎስ የሰበካቸውና ያሳደጋቸውን፡ በወንጌል እንክብካቤ ተደረገላቸው። አያችሁ?

**... ለኤፌሶን፡ እና በክርስቶስ ላሉት ምእመናን...**

95 በክርስቶስ ውስጥ ያሉት ማለት እነዚህ ናቸው። በክርስቶስ ውስጥ እንዴት እንገኛለን? "በአንድ መንፈስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፡" እርሱም የክርስቶስ አካል ነው።

**ከእግዚአብሔር ከአባታችን... ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጸጋና፡ ሰላም፡** ለእናንተ **ይሁን።**

**የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፡ በክርስቶስ** ኢየሱስ **በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ** የባረከን፥

96 አሁን አሰቡት! በሰማያዊ ጸጋን ሁሉ ባርኮናል፡ (እንደ አማኞች፡ እንደ ተመረጠች ቤተ ክርስቲያን፡ እንደተጠራች፡ እንደተለየች) በክርስቶስ ኢየሱስ አብረን ስንሰበሰብ፡ እንባረካለን። በቅዱስ መንፈሱ አተመን፡ አሁንም ወደፊት ለእኛ ያሰበውን ነገር ሁሉ እየገለጠልን ይገኛል። አሁን ወደ ሰባቱ ማሕተሞች አልፈናል።

**ዓለም ሳይፈጠር በእርሱ ዘንድ እንደመረጠን፡ ቅዱሳን እና ያለ ነቀፋ... በፍቅር እንሆን ዘንድ ነው፥**

**... እንደ በጎ ፈቃዱ በኢየሱስ ክርስቶስ፡** ለራሱ **ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰኖናል**

97 እንዴት የሚያምር ሀሳብ ነው! አንድ ደቂቃ ማንበባችን እንቀጥል። በተለይ ወደ 12ኛው ቁጥር፡ እና 13ኛ፡ 14ኛ መድረስ እፈልጋለሁ፥

**ይኸውም** በእርሱ **አስቀድመን ተሰፋ ያደረግን እኛ፡ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው።**

**እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፡** ይኸውም **የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም፡ በእርሱም... ካመናችሁ... በኋላ፡ በተሰፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ፡**

98 "ካመናችሁ በኋላ።" ኦህ፡ የባፕቲስት ወንድሜ ሆይ፡ እንዴትስ እንዲህ አይደለም ትላለህ? **ባመንን** ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንቀበላለን ታላልችሁን? እሱ ያለው፡ "ካመናችሁ **በኋላ** በተሰፋው መንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ።" ልብ በሉ፡-

**እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፡ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል።**

99 ስለዚህ፡ አሁን **ማህተም** ምን ማለት እንደሆነ ደርሰንበታል "በእግዚአብሔር ዘንድ የተፈጸመ፡ አስቀድሞም የተረጋገጠ ነገር ነው።" ስለዚህ እያንዳንዱ አማኝ ከመጀመሪያ ጀምሮ በዚህ የተሰፋ ቃል ታትሟል፡ ምክንያቱም ዓለም ሳይፈጠር በፊት ልጆች ልንሆን አስቀድመን ተወስነናል። ዓለም ከመጀመሩ በፊት! ኦህ፡ እንዴት ያለ ተሰፋ ነው! ያም ጸንተን እንድናርፍ ያደርገናል። ወዲህና ውዲያ ያልተፍገመገመ ነገር ግን በክርስቶስ የጸና፡ እርግጠኛ የሆነ ተሰፋ፡ የነፍስ መልህቅ ነው። "ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወስኖናል።" ኦህ፡ እንዴት ድንቅ ነው! ይሄ ደስ ይለኛል፡ "ያለቀለት ሥራ" ከእግዚአብሔር ጋር።

100 አሁን፡ ሌላ ከቅዱሳት መጻሕፍት ልጥቀስላችሁ። "አስቀድሞም የወሰናቸውን፡ እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፥ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ፡ አጸደቃቸው፥ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ፡ አከበራቸው።" ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር፡ በታላቅ አሳቡ፡ ቤተ ክርስቲያኑን አስቀድሞ አይቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ልጆች እንድትሆኑለት አስቀድሞ ወስኖታል፡ ይህም በዘመኑ መጨረሻ የዘላለም ሕይወት እንዲሰጣቸው ነው። እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው! ወንድም ኔቪል ሆይ፡ ይህ በጣም ጥሩ ስሜት እንዲሰማኝ አድርጎኛል። አንተ አይደለህም? ኧረ፡ አዎ። ልጅነት በኢየሱስ ክርስቶስ ደም!

101 አሁን፡ እየቀጠልን ልብ በሉ። አሁን፡ ያለቀለት መሆኑን አውቀናል-... ከበጉ ጋር አስቀድሞ ተወስነናል። መንፈስ ቅዱስ ማኅተማችን ነው። **ቀብድ** ሲባል "ብዙውን ወደፊት ይመጣል" ማለት ነው። አሁን ያለን የዋናው ቀብድ ብቻ ነው። ቀብድ ማለት ቅድመ ክፍያ ማለት ነው (ኧረ፡ ደስ ይላል!)፡ ማንም እንዳይነካን በደንብ አጥብቆ የሚይዝልን እና የሚጠብቅልን ቅድመ ክፍያው ነው። የልጅነታችን ቀብድ ነው። አሜን። መንፈስ ቅዱስ አሁን በልባችን ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ቀብድ ነው (የታተመ)፡ ልጆች የመባል የልጅነት ሂደት በመንገዱ በመጨረሻ ላይ እነሆ ይጠብቀናል። የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች!

102 አሁን በፍጥነት፡ ወደ ሌላ ቃል እንለፍ፡ በዚህ ሌላኛው ገጽ ላይ ጽፌዋለሁ። ሮሜ 8፡22 ላይ፡ እጅግ ድንቅ ይመስለኛል። አሁን፡ ትላንትና ጥናት ላይ ሳለሁ፡ እዚህ ለመጥቀስ የምፈልጋቸውን ጥቂት ቅዱሳት ቃላት ጻፍኩ።

**... ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና** በምጥ **መኖሩን እ—እናውቃለንና።**

**እነርሱ ብቻ አይደሉም፡ ነገር ግን የመንፈስ በኲራት ያለን፡ ራሳችን ደግሞ፡** የሰውነታችን **ቤዛ የሆነውን ልጅነት፡ እየተጠባበቅን፡ ራሳችን በውስጣችን፡ እንቃትታለን።**

103 ኦህ፡ አይታችሁታል? "ፍጥረት ሁሉ ይቃትታል፡" አለ ጳውሎስ። ሁሉ ይቃትታል። ዛፎቹ እንዴት እንደሚታገሉ ተመልከቱ። አበቦችን ለሕይወት እንዴት እንደሚታገሉ ተመልከቱ፡ ውርጩ እንዴት እንደሚገርፋቸው። ዛፎች ለእግዚአብሔር ክብርን ለመዘመር ቅርንጫፎቻቸውን ለመያዝ እንዴት እንደሚታገሉ ተመልከቱ። አያችሁ? ነገር ሁሉ፡ ተፈጥሮ ሁሉ፡ እንስሶች፡ አእዋፋት፡ ከጠላት በፍጥነት በርረው ያመልጣሉ፡ ነገር ሁሉ ይቃትታል። "እኛም እንዲሁ፡" አለ ጳውሎስ፡ "የሰውነታችንን ቤዛ እየጠበቅን፡ እኛም፡ አብረናቸው፡ እንቃትታለን።"

104 ግን **አሁን**! **አሁን**! እስከ **አሁን** ድረስ ላለፉ ዘመናት ሁሉ ሲቃትቱ ኖሩ! **አሁን** የርስታችንን ቀብድ እነሆ ተቀብለናል! ኦህ፡ ማይ! ምን አለን? እግዚአብሔር ሕያው ስለመሆኑ ማረጋገጫ አለን። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ስለመሆኑ ማስረጃ አለን። እኛ (በአካላችን ውስጥ) እግዚአብሔር እንዳልተወን፡ እኛ የእርሱ እንደሆንን እርሱም የእኛ እንደሆነ፡ የሚያሳይ ማስረጃ አለን፡ አሁን ግን "አባ፡ አባት" ብሎ፡ የሚጮኽ መንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆነናል። ከእንግዲህ በክርስቶስ መልህቅ ጸንተናል። ያን ከእኛ ሊወስድብን የሚችል ነገር የለም።

105 አሁን፡ ዛፎች ያንን አላገኙም፡ ተፈጥሮም አላገኘም፡ እኛ ግን ገና እስካሁን የልጅነት ጊዜያችንን ሙሉ በሙሉ አልተቀበልንምና አብረናቸው እንቃትታለን። እኛ ግን ከዓለም ነገሮች ተለቅመን የተወሰድን ስለ መሆናችንን የሚገልጽ፡ ቀብድ ተቀብለናል አሁንም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሆነናል። ምን ዓይነት ሰዎች መሆን ይገባን ይሆን? ኦህ፡ ማይ፡ ያንን ሰናስበው! እስኪ አስቡት!

106 አሁን ቀብዱን ተቀብለናል፡ መንፈሳችን ግን ሙሉ በሙሉ ልጆች እስክንባል ድረስ ይቃትታል፡ ይሁን እንጂ ቀብዱን ተቀብለናል። መንፈስ ቅዱስን ስንቀበል፡ የሙሉ ልጅነታችን ወይም የሙሉ መዳናችን ቀብድ ነው። ኧረ፡ እንዴት ድንቅ ነው! ይህ ነገር ደስ ይለኛል። በጣም ጥሩ።

107 የልጅነታችን ሙላት በመጠባበቅ እንገኛለን። ይህ መቼ ይሆናል? በመጀመሪያው ትንሳኤ ላይ ይሆናል። ይህም ሰውነታችን አሁን ካለበት እርኩስ ፍጥረት ተቀይሮ እንደ እርሱ ያለውን የከበረው አካል የሚኖረን ያን ጊዜ ነው፡ "እርሱንም እንዳለ እናየዋለንና፡ እኛም እንደ እርሱ እንሆናለን።" እርሱ ሲገለጥ፡ በምስሉ እንገለጣለን። የእርሱን የሚመስል አካል ይኖረናል፡ የከበረ ክብር ያለው አካል ይኖረናል። ያን ጊዜ የህይወት ፈተናዎች እና ውጣ ውረዶች በሙሉ ከእንግዲህ ወደማይኖሩበት ወደ ጥቃቅን ነገሮች ተቀይረው ይጠፋሉ።

108 እና አሁን የምንቃትትባቸው እነዚህ ምድራዊ ድንኳኖች፡ ቀብዱን እየጠበቅን እንገኛለን—ያንን ቀብድ... የሙላት መዳናችንን በሙላት እስኪመጣ ድረስ እንጠብቃለን። አሁን ግን በእነዚህ የሸክላ ድንኳኖች ውስጥ

እስካሁን እዚህ ድረስ መነሳታችን የሚነግረን ነገር አለን። ኣሜን። ቀብድ ምንድነው? ወንድም ዳውች ሆይ፡ ዋናውን መያዣ የሚሆን አነስተኛ ቅድመ ክፍያ። ቀብድ ይባላል። አሁን፡ ያን ጊዜ የዓለምን ነገር ስንወድ፡ ኃጢአትን ስንሠራና የዓለምን ነገር ስንሠራ በነበርን ጊዜ፡ ስለ እግዚአብሔር አይገደንም ነበር፡ ከእርሱ ተለይተን፡ ያለ እግዚአብሔር፡ ያለ ክርስቶስ ሆነን፡ በዓለም ውስጥ መጻተኞች ነበርን፥ አሁን ግን፡ እግዚአብሔር መንፈሱን ልኮልናልና ከእነዚያ ነገሮች ከፍ ከፍ ተደርገናል። አሁን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን የምናውቅበት፡ ቀብድ ተቀብለናል። አሜን!

109 እዚህ ጋር፡ ይህንን **እንደዚህ** ለማሳየት ሰሞክር። ተራ ኃጢአተኛ የሚርመሰመስበት ሰፍራ **እዚህ** ሰር ነው። አሁን፡ ክርስቲያኑ ግን ከዚህኛው ይልቅ፡ ከአሸንክታቦች በላይ በትንሹ ከፍ ብሎ ይወጣል። የማዳኑ ቀብድ ማለት ይህ ነው።

110 ስለዚህ፡ ራእዮች የሚሰሩላችሁን ነገሮች... ይህ ሲሆን ታውቁት ዘንድ። ስለዚህ ተባበሩኝ፡ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው፡ ሌላ እንዲኖረኝ በፍጹም አላስብኩም ነበር። እንዲህ ከሆነ፡ ለራሴ እይዘዋለሁ፡ አያችሁ፡ ምክንያቱ የሚያደርገውን ነገር እኔ እውቀዋለሁ። ህዝቡ ለእንዲህ ዓይነቱ አገልግሎት ዝግጁ ሰላልሆነ፡ እንዲሁ መተው ያስፈልጋቿል፡ አያችሁ፡ ወደዚህ መመለስ። ይሁን እንጂ በድጋሚ ወደ መስኩ ከተመለስኩ፡ ወንጌላዊ እሆናለሁ። ግን ወደዚህ ተመልከቱ። እዚህ ጋር፡ እዚህ ወደላይ፡ ወደዚህ ስትመለሱ፡ እዚህ ጋር ወዳለው ሰማያዊ ከፍታ ትወጣላችሁ። እዚያ አካባቢ በከፍታው ባሉ አድማሶች ዘንድ ትኖራላችሁ። ሰው ከሚያሰበው ከምንም ነገር በላይ፡ ከማናቸውም ነገሮች በላይ ትወጣላችሁ። ይህም በዚያ ወዳሉ ክፍተቶች ዘንድ ያደርሳችኋል።

111 ነገር ግን፡ እንደምታዩት፡ በመንፈስ ቅዱስ በኩል፡ የርስታችንን ቀብድ የሆነውን፡ አሁን ተቀብለናል ምክንያቱ ከዓለም ነገሮች ሁሉ ከፍ ስለተደረግን ነው፥ እና ከአለም ጋር በትክክል እየተጓዝን፡ እኛ ግን ከአለም በላይ የወጣን ነን! ወንድም ኔቪል ሆይ፡ እግዚአብሔር ይማረን ለሕያው ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ይህን ይሰጥ...

112 ስለ ቤተ ክርስቲያን፡ ማለት ውቧ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለውን ነገር ወደ ማሰብ ከደረሰን፡ እንግዲያውስ፡ "ከአለም ነገሮች ጋር ለማነፃፀር እየሞከርን ነው። ከእነርሱ ይልቅ የተሻለ የቤዝቦል ቡድን እንዲኖረን እየተመኘን ነው። ከሌሎች የተሻለ—ህንጻ ይኑረን እያልን ነው። የተሻለ የቡንኮ ጨዋታ ሊኖረን ይገባል እያልን ነው። **ይህ** እና **ያ**፡ ወይም **ያ** የተሻለ ሊኖረን ይገባል እያልን ነው።" ለምን፡ ከዓለም አሸንክታብ እና ከመብለጭለጭ ጋር ለምን እናነጻጽረዋለን? እኛ እንደዚያ አይደለንም... ወንጌል **ብልጭልጭ** ሳይሆን፡ **መብራት** ነው። በመብለጭለጭ እና በመብራት መካከል ልዩነት አለ።

113 ስለዚህ፡ እንደተናገርኩት፡ አንዱን—አንዱን ሬሳ ከማቆያው ወደ ሌላ ማቆያ እየወሰድን፡ እንቅበዘበዛለን፡ ይህ ማለት አባላት መቀየር እና የመሳሰለ ነገር ማድረግ ነው። ታዲያ፡ ይህ ምን ይጠቅመናል? ትልልቅ ካቴድራሎች፡ ትላልቅ እና ውብ ቦታዎች፡ እንዲያብረቀርቅ እናደርገዋለን፡ "የእኛ ከሜቶዲስት የተሻለ ወይም ከመጥምቁ የተሻለ ሊሆን ይገባል፡ የሁላችንም ውድድር ከካቶሊክ ጋር

ነው፡ እና የቡንኮ ጨዋታዎች እና ፓርቲዎች እና እራት እና መዝናኛዎች፡ እና ሁሉም ነገር እናደርጋለን።"

114 ቤተ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ፈጽሞ ልትወዳደር አይገባትም። የእናንተ እና የቤተ ክርስቲያናችሁ መዝናኛ ከማሶኒክ ሎጅ ጋር ወይም ከሌሎቹ ከማናቸውም ሰዎች—ጋር በምን መንገድ ታወዳድሩታላችሁ? ያ'ማ ሜዳቸው ነው። በገዛ ሜዳቸው አትጫወቱ።

115 እኛ ግን በእነርሱ ዘንድ የሌለውን ነገር አለን! ኢየሱስ አለናን። የሆነ ነገር ከፈለጉ ወደዚህ ይምጡ። በክርስቶስ ጽኑዎች ሁኑ። ኢየሱስ አለን። እነርሱ የላቸውም... ወደዚህ እስካልመጡጅ ድረስ ኢየሱስን አያገኙትም። እኛ ወደዚያ ከሄድን፡ ከሜዳው ውጪ እንሆናለን።

116 ለማብለጭለጭ እንዳትሞክሩ። አብሩት! የምታበሩት እናንተ አይደላችሁም፡ እርሱ በእናንተ አልፎ እንዲበራ አድርጉት። አያችሁ?

117 ትንሹ የሚያበራው ትል፡ ማብራት ስለፈለገ አያበራም፥ ስለሚያበራ **እንጂ**፡ ስለዚህ በውስጡ የሚያበራ ነገር አለው። በራሱ ውስጥ ነው፡ ራሱ ያደርገዋል፡ በውስጡ ያለው ነገር በእሱ ውስጥ አልፎ ያበራል።

118 እንግዲህ፡ መንፈስ ቅዱስም እንዲህ ነው። የተለየ፡ ልዩ ነገር፡ ከሌላው የተለየ ነገር ያለው መሆን አይጠበቅብንም፡ ቀለል አርጋችሁ እግዚአብሔርን የመምሰል ህይወት ኑሩ እግዚአብሔር ራሱ በእናንተ ዘንድ ይኑር። የወንጌል ብርሃን ያ ነው። አያችሁ? ብልጭልጭ አይደለም፡ **ብልጭልጭ፡** የሚብለጨለጭ ነገር፡ ዝንጀሮዎች እንደዚህ ባሉ ነገሮች ላይ እንዲዘሉ ያደርጋቸዋል። ታውቃላችሁ፡ አንድን ነገር ፍለጋ ሁልጊዜ ይዘላሉ "ያም የሚብለጨለጭ ነገር ነው።" **የሚበራ** ነገር ግን "ለሰላሣ፡ ጣፋጭና መልካም የ—የመንፈስ ቅዱስ ነው።"

119 አሁን ትንሳኤን እየተጠባበቅን ነው። እሺ፡ አሁንስ፡ ገባችሁ? እስኪ "ቀብድ" ስል፡ ከገባችሁ፡ "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤው "ኣሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ምን ስለሆንንን... ከፍ—ከፍ ስለተደረግን ከሞት ወደ ህይወት እንደተሻገርን እናውቃለን። ሰዎችን ሁሉ እንድንወድ፡ ከዓለም ነገር ከፍ ከፍ ተደረግን እንጂ፡ በራሳችን ከፍ ከፍ አላልንም። እግዚአብሔርም ይወደናል፡ እኛም እናውቃለን። ስለዚህ በህይወታችን ላይ ስንመለከት መንፈስ ቅዱስ ራሱ እንደሆነ ይገባናል፡ ምክንያቱ ከእንግዲህ ስለ አለም ነገሮች አንጨነቅምና። አያችሁ? ይኸውላችሁ። ዓለምን ወይም የዓለምን ነገር መውደድ በእናንተ ዘንድ እስካለ ድረስ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ገና በእናንተ ውስጥ የለም። አያችሁ? ከዚያ በላይ እስከወጣችሁ ድረስ ግን፡ ርስታችሁ መቀበላችሁን ታውቃላችሁ፡ አያችሁ፡ ወደ ሙሉ ቤዛነታችሁ—መንገድ ይዛችኋል ማለት ነው።

120 አሁን፡ ግን፡ ተመልከቱ፡ አስቀድመን ይህ እስከሌለን፡ ኢየሱስን እስካላየነው ድረስ ግን... ይህ አይመጣልንም። እርሱ ሲመጣ፡ እንደ ሰውነቱ ያለ አካል ይኖረናል እርሱንም እንመስላለን። በጣም ጥሩ።

121 አሁን፡ እዚህ ጋር አንድ የጠፋብን ነገር እንመለከታለን፡ ምክንያቱ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚናገር፡ ማለት፡ በዚህ በተቤዠን—መጽሐፍ ውስጥ። የተቤዠን ከምንድነው? ከጠፋንበት ነገር። ከመቤዤታችሁ በፊት፡ የሚቤዤን ነገር መኖሩ

ያስፈልግሃል። ድሮ የነበረን ርስት ሁሉ—ተቤዥቶልናል። ይህ ማለት አሁን የሌለን ነገር ከዚህ በፊት ግን የእኛ የነበረ ነገር አለ ነው፡ ስለዚህ ይህ በግ ሊቤዠን መጣ። አያችሁ? እኛ የጠፉንበት አንዳች ነገር አለን።

122 አሁን ልብ በሉ። የጠፋብን ምን ነበር? እንግዲህ፡ አዳም የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ተሰጠው፡ ከዛፉ እስኪበላ ድረስ የዘለአለም ህይወት ነበረው። ሌላ ደግሞ ምድር... የአዳም—ርስት እንደነበረች አስተውለናል። በምድር ላይ... እንደ ታናሽ አምላክ ይኖር ነበር። ምድር የእሱ ነበረች። ሁሉም ነገር በእጁ ተሰጠው፡ የፈለገውን ነገር ማድረግ ይችል ነበር። ስያሜን ያወጣል፡ ይጠራታል፡ ማድረግ የፈለገውን ሁሉ ያደርግ ነበር። እውነተኛ የእግዚአብሄር ልጅ ነበር።

123 አሁን፡ በውድቀት ምክንያት፡ አዳም የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩን አጣ። ለሰይጣን አሳልፎ ሰጠው። የባለቤትነት ማረጋገጫውን ሰይጣን ወሰደበት። አዳም በጣም ሰነፍ ሆነ፡ መብቱን መዋጀት ስላልቻለ መብቱን መዋጀት ተሳነው። ሰይጣን ግን፡ በትክክል ባለቤት ባይሆንም፡ ተቆጣጠራት፡ ስለዚህ የዚህ ምድር አምላክ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስም ይናገራል። ተቆጣጥሯታል። ይህ ግን በመብት ደረጃ በትክክል—የሱ—የራሱ ስለሆነች ሳይሆን፡ እንዲሁ ተቆጣጥሯታል። አሁንስ ገባችሁ? ሰይጣን ተቆጣጠራት፡ በእጁ ውስጥ አስገባት። ሞት በእጁ ነው፡ ምድርም በእጁ ናት፡ ዓለም የእርሱ ነው፡ እያንዳንዱ መንግስታት ሁሉ የእርሱ ናቸው፡ መላውን ዓለም እና በዓለም ውስጥ ያለውን ሁሉ ያስተዳድራል ይቆጣጠራል። ሰይጣን ያስተዳድራታል!

124 እኛ ግን የአለም አይደለንምና እግዚአብሔር ይመስገን። አያችሁ? ስለዚህ—ተመልከቱ። አያችሁ? እኛም... ቤተ ክርስቲያን ማለቴ ግን አይደለም፥ ቤተ ክርስቲያንን አይገዛትም። የሚገዛው አለምን ብቻ ነው። እርሱም የኔ ናቸው ብሏል፡ የአለም አምላክ ነው። ኢየሱስም እንዲሁ እንደሆነ መሰክሯል፡ ደግሞም ነው። “የዚህ ምድር አምላክ ነው፡ የሰዎችን ዓይንም አሳውሯል፡” የዚህ ምድር አምላክ። እርሱ የሰማይ አምላክ ነው። አሁን በትክክል የዚህ ባለቤት አይደለም። ባለቤት አይደለም።

125 እርሱ ግን... አዳም ግን የባለቤትነት ማረጋገጫውን፡ ለዚህኛው ጥሎለታል፡ ርስታችን የነበሩ ነገሮች በሙሉ፡ የዘላለም ሕይወትና የምድር ርስት ሁሉ። ኢየሱስ በማቴዎስ ምዕራፍ 5 ላይ፡ “የዋሆች ብፁዓን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና፡” አለ። አያችሁ? አሁን፡ አልያዟትም።

126 እናም፡ ተመልከቱ፡ ለአዳም ወይም ለዘሮቹም አልነበረችም። የአዳም ዘርም እንዲሁ፡ ሁሉንም ነገር ጥሏል። የአዳምን ዘር አይደለችም። የቱንም ያህል ይህን ዓለም ለማስዋብ ብንሞክርም፡ እንዲሁም የቱንም ያህል ጥሩ ቤቶችን እና ነገሮችን ለመሥራት ብንሞክርም፡ አሁንም የአዳምን ዘር አይደለችም። አይደለችም፡ ጌታዬ። ወደ አዳም ዘር አልሄደችም፡ በጭራሽ፡ ጌታዬ፡ ምክንያቱ ሰይጣን፡ አንዳች ሳያስቀር ወስዶ ቆልፏታል። በትክክል! አዳም አጥቷታልና።

127 አሁን፡ ኦህ፡ ማይ! አዎን፡ ብዙ ነገሮች ማለት ይቻላል። አሁን ጊዜአችሁን መውሰድ አ—አልፈልግም፡ ጥምቀት፡ ማድረግ ይኖርብናል። እሺ።

128 ምንም ቢይዛትም እንኳ በሙብት ደረጃ ግን ባለቤት አይደለም፡ ባለቤት ሰይጣን ነው። ትክክለኛው ባለ ሙሉ ሙብት ባለቤት—ባለ ሙሉ ሙብት ባለቤት—ባለቤት የሆነው ከጣለ፡ መቤዠት የሚችልበት ብቸኛ መንገድ አንድ አለ። ይህም፡ በቅርብ ዋርሣ በኩል ነው፡ በሙሉ ሙብት ሊቤዣት የሚችለው ብቸኛው እርሱ ነው። እንግዲህ፡ በርግጥም፡ ይህ በኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል መወለድ ውስጥ ሆኖልናል።

129 አሁን፡ እዚህ ጋር አንድ ነገር መናገር እፈልጋለሁ። ወደ ኋላ መመለስ የምንፈልገው የመጀመሪያው ነገር፡ እዚህ ጋር ወደ በብሉይ ኪዳን—ውስጥ ከተመለስን፡ እዚህ አካባቢ ላይ እንደጻፍኩት ትዝ ይለኛል፡ ዘሌዋውያን 25 ላይ። ማስታወሻ ለምትጽፉ ሰዎች፡ የመቤዠትን ህግ፡ በዘሌዋውያን 25፡23 እና 24 ላይ ታገኙታላችሁ። እግዚአብሔር እስራኤልን ምድሪቷን... በኢያሱ ባከፋፈላቸው ጊዜ... ሰው ማንኛውንም ነገር ለመዋጀት፡ እያንዳንዱ ነገድ እና እያንዳንዱ ሰው እንደ—ግዛት ይሆንለት ዘንድ ልጆቹ የሚወርሱበት መሬት ተሰጥቷቸው ነበር።

130 እና፡ አንድ ሰው ድሃ በመሆኑ ምክንያት ያለውን ነገር በሌላ ሰው ከተያዘበት፡ ይህን... የሚቤዥለት ብቸኛው መንገድ በቅርቡ ዋርሣ ዘመድ ነው። በመጨረሻው ግን መመለሱ የማይቀር ነው። ይህ ሰው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ይይዝበታል። ወደ ዋናው ባለቤት መመለሱ ግን አይቀርም። በትክክል! ወደ ዋናው ባለቤት መመለስ አለበት። ከ... ከይሁዳ ነገድ የሆነ አካል፡ ለምሳሌ እንዲህ ቢገጥመው... ለምሳሌ ይህ ነገር የአባቱ ዕጣ ፈንታ ቢሆን፡ ቀጣይ ወራሽ እርሱ ቢሆን፡ ወይም የቅርቡ ዋርሣ ቢወስደው። ይሁን እንጂ፡ አሁን፡ በሱ ነገር ላይ ሙብት የሚኖረው የለም... ይይዙበታል፡ ሰነዱን ይይዙበታል። ዕዳው እስኪከፈል ድረስ የባለቤትነት ሰነድ ይይዙበታል፡ ትክክለኛው ሰው እስኪመጣ ግን፡ ያ ሰው...

131 ለምሳሌ፡ እንበልና፡ አንድ ንብረት ነበረኝና በጋጣሚ ከእጄ ይወጣል፡ እና ከይሁዳ ነገድ ለሚሆነው፡ ለሌላ ሰው፡ ወይም መጻተኛ ለሚሆነው ሰው ለወንድም ኔቪል ሸጥኩለት። ስለዚህ እሱ በሙሉ ሙብት፡ ባለቤት ይሆናል፡ እየመጣ ያርሰዋል ፍሬውንም እየመጣ ይጠቀምበታል፡ ወዘተ፡ ይሁን እንጂ የያዘው የባለቤትነት ሰንድ ብቻ ነው። “የራሱ ሊሆን አይችልም፡” በእስራኤል ዘንድ ሕጉ እንደዚያ ነበር። አሁን በዘሌዋውያን 25 ላይ—እንብቡ፡ በዚያ ውስጥ ባለ ሙሉ ሙብት ባለቤት እንደማይሆኑ ታያላችሁ፡ ሰነድ ብቻ **ይይዛል**።

132 እና፡ አሁን፡ ለምሳሌ፡ ልጄ ቢሊ... እዚያ ጋር፡ የእኔ የሆነውን ነገር፡ ይፈልጋል... መጥቶም ይህን መሬት ይገዛዋል። እንግዲህ፡ እንግዳው ሰው፡ ወይም ወንድም ኔቪል ወይም—ወይም ሌላ ሰው የባለቤትነት ደብተሩን ከያዘ፡ የያዘው ሰንድ ብቻ ነው... አሁን፡ ይህ የቅርብ ዋርሣዬ ዘመዴ ከሆነ፥ በደም ዘመዴ ነው፡ ከዚያ በኋላ ሊይዘው አይችልም። አይችልም፡ ጌታዬ። ዋጋው ሙሉ በሙሉ ከተከፈለ በኋላ፡ አዎን፡ ጌታዬ፡ የመመለስ ግዴታ አለበት፡ ለምሳሌ፡ የንብረቱን ዋጋ የሆነውን ሃያ-አምስት ሺህ ዶላር፡ ከተሰጠው ይመለሳል።

133 ከዚያ፡ በኋላ፡ እንበልና፡ ወንድም ቶኒ መጥቶ እንዲህ ቢል፡ “ወንድም ኔቪል፡ የወንድም ብራንሃምን ንብረት እገዛለሁ ቢልም።” መግዛት አይችልም።

ወንድም ኔቪል “አይ፡ ጌታዬ፡ መሸጥ አልፈልግም፡” ይለዋል።

“ለማንኛውም፡ ስንት ትከፍላለህ? ”

“ሃያ-አምስት ሺህ።”

“እሺ፡ ስላሣ-አምስት ሺህ ል—ልሰጥህ። **እንዲህ-እና-እንዲያ** ልሰጥህ።”

“ምንም ያህል ብትል አይገደኝም። መሸጥ አልፈልግም፡ አቆየዋለሁ።”

134 ነገር ግን ቢሊ ፖል መጥቶ “የአባቴን ንብረት እፈልጋለሁ፡ እነሆ ሃያ-አምስት ሺህ፡” ይለዋል። ያኔ ለመልቀቅ ይገደዳል። ይህ ትክክል ነው፡ ምክንያቱ ሕጉ እንደዚያ ነው።

135 ኦህ፡ ሃሌ ሉያ! እህም! ክርስቲያኖች ሆይ እንደምታዩት ተሰፋ አደርጋለሁ። እኛ የምድር ጨው ነን። እግዚአብሔር ይህን ለልጆቹ ሰጠ። በተፈጥሮ ሁሉ ላይ፡ በእንስሳት ሁሉ ላይ፡ በህይወት ሁሉ ላይ በሁሉም ላይ ስልጣን ሰጠን። አባታችን፡ አዳም ግን፡ ለሰይጣን አሳልፎ ሰጠው። ወደ ማን ግን ይመለሳል? ይህን ሁሉ ወደ ሰራው፡ ወደ ሙሉ ባለቤት። አሜን!

136 ዮሃንስ “ምርር ብሎ ማልቀሱ” አይገርምም፡ ሊቤዥ የሚችል አንድም ሰው አልነበረምና። ሰውዬው ብቁ ሊሆን ይገባዋልና። ዮሐንስ “መጽሐፉን ሊወስድ ወይም ሊመለከተው ወይም ማኅተሙን ሊፈታ የሚችል ባለመገኘቱ እምርሬ አለቀስኩ፡” አለ። እርሱም “አንድም… አንድም ሰው በሰማይ አልተገኘም፡ በምድር ላይም አልተገኘም፡ ከምድር በታችም ማንም ሰው አልተገኘም፡ በሁሉም ቦታ አልነበረም፡” አለ።

137 “አንድም ሰው አልተገኘም።” እንግዲህ፡ መላእክትን አልናቀም። ልብ በሉ፡ ይህ ምድር ለመላእክት አልተሰጠምና። የሰው ልጅ ርስት ነው። ገብርኤል ይችል ነበር፡ አዎን፥ የሆነ አካል ይችል ነበር፡ ሚካኤልም እንዲሁ ብቁ ሊሆን ይችል ነበር። እንደ… ይህን ለማድረግ ብቃት ሊኖራቸው ይችላል። በሰው ዘንድ ግን ብቁ የሆነ አልነበረም። አያችሁ? በዚህም ምክንያት ዮሃንስ በታላቅ ድምጽ አለቀሰ።

138 አንድ ሰው ሲናገር “ራሱን ብቁ እንዳልሆነ ስላወቀ ነው፡” ብሏል። እንደዚያ ግን አይደለም። ሰውየው በመንፈስ ቅዱስ ተጽእኖ ስር ስለነበር፡ እንደዚያ አይነት ስህተት መስራት አይችልም። ይሁን እንጂ—እርሱ… እ—እ—እ… የእሱ ብቁ አለመሆን ብቻ ሳይሆን፡ ሌላ ብቁ ሊሆን የሚችልም አላገኘም ነበር።

139 እና ያን ጊዜ እንዲህ አለ፡ “ከሽማግሌዎቹ አንዱ ወይም ብርቱ መልአክ መጣና፡ እንዲህ አለኝ፡ ‘ከይሁዳ ነገድ የሆነ አንበሣ አለና፡ አታልቅስ፡’” (አሜን!) “‘የዳዊት ሥር፡ ድል ነስቷልና!’” አሜን! በሌላ አነጋገር፡ “‘አሸንፏል።’” “‘መጽሐፉን ሊወስድ ይገባዋል!’” ኣሜን።

140 እስከዚህች ጊዜ ድረስ እንዳለየው፡ አስታውሱ። ለምን? በዚያ ባለው ዙፋን… እግዚአብሔር ዙፋን ላይ፡ ስለተቀመጠ ነው። በመቅደሱ ውስጠኛው ክፍል ላይ ስለነበረ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ገና አላየውም፡ ስለዚህ ዮሐንስ አንበሣ ሲመጣ… ማየት ፈልጎ ነበር፡ ይህን እንጂ በግ አየ!

141 ይኸውላችሁ፡ ወንድሞች ሆይ። በትህትና፡ በመልካምነት፡ ድል በምንነሳበት በመንፈስ ቅዱስ። ድል መንሣት ታላቅ እና ኃያል አዋቂ

በመሆን ሳይሆን፡ እራስን ዝቅ በማድረግ ነው። በሁሉም እየተመታ ነገር ግን የክርስቶስ ባርያነቱን የማይተው ሰው፡ እርሱ ድል ነሺ ነው።

142 አሁን፡ እንዲህ አለ፡ “ድል ነስቷልና። እርሱም መጽሐፉን ሊይዝ ሊከፍተውም ማኅተሞቹንም ሊፈታ ብቁ ነው።”

143 አሁን፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ ምናልባት ዛሬ ላይሆን ይችላል፡ ግን እነዚህ ሰባት ማህተሞች ምን እንደያዙ፡ ምን እንዳደረጉ ለማወቅ እንሞክራለን።

144 አሁን፡ በጥቂቱም ቢሆን “መቤዠትን” እንውሰድ። ሰውዬው—ከመ... ቤዛ ከመሆኑ በፊት፡ ከሁሉ በፊት፡ ብቁ መሆን አለበት፡ ትክክለኛ አይነት ሰው መሆን አለበት። ስለዚህ ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግልና በተወለደ ጊዜ ሆነ፡ እርሱ አምላክ ነውና፡ በድንግልና የተወለደ ነው። እርሱ ራሱ ሰው የሆነ አምላክ ነበር፡ የሰው ስጋ የለበሰ አምላክ ነበር። ስለዚህ ብቁ ሊሆን ይገባው ነበርና፡ ድንግል የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቁ እንዲሆን አስችሎታል። አሁን፡ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት መሄድ ከፈለጋችሁ፡ ወደ አንደኛ ጴጥሮስ 1፡18 እስከ 20 ድረስ፡ ያለውን እናገኛለን፡ ቃሉን እስከ ታች ድረስ ካያችሁት። ብቁ ሊሆን ይገባው ነበር። እንዲሁም ሆነ፡ የሰውን አምሳል ለራሱ ወሰዷልና። ሰውም ሆነ፡ እግዚአብሔር ራሱ ዋርሳችን ሆነልን። በዚያም ውብ በሆነው ክፍል ውስጥ ያሕዌ የአምላክ ሥጋን ሆኖ በመካከላችን ማደሩን እናገኛለን። አሜን።

145 “ድል ነስቷል።” እግዚአብሔርም የሰውን ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር መጣ፡ ሕፃን ልጅ ሆኖ ተወለደ፡ በመካከላችንም ተመላለሰ። በቅዱስ ደሙም ድል ነሳ።

146 አሁን፡ በብሉይ ኪዳን ዘንድ፡ አንድ ሰው የራሱ የነበረውን ነገር ሲዋጅ፡ ምን ያደርግ ነበር? ሽማግሌ ይወስድና፡ አስር ሽማግሌዎችን ይዞ፡ ወደ ደጅ ይሄዳል በዚያም ሊያደርግ ያሰበውን፡ ከዚህ በፊት የጠፋበትን ነገር መዋጀት እንደፈለገ ያስተዋውቃል፡ ማንነቱንም አሳይቶ፡ ምሥክርነት ይሰጣል። እዚህ ጋር አንድ ውብ ታሪክ እናገኛለን (አንድ ትንሽ ማስታወሻ እዚህ ጽፌአለሁና... ዛሬ ጠዋት ፍርሃት ስለነበረብኝ፡ አልረሳሁትም።) ታሪኩም ስለ ሩት፡ እና ስለዘመዷ ቦዔዝ ነው። በቅርብ ጊዜ ተምረነዋል። የዚህ ማረፊያ ሶስት ደረጃዎችን አሁን እንድታስተውሏቸው እፈልጋለሁ።

147 የቤተክርስቲያንን ማረፊያም አንድ አይነት ነገር ነበርና፡ ልብ እንድትሉት እፈልጋችኋለሁ። አሁን፡ ተከታተሉ። የምናገኘው አንደኛው ሰፍራ፡ ሁላችንም ያገኘ፡ **የዋርሣ ቤዛ** የሚለውን ስብከት እንደሰማነው፡ ቤዛ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ስጋ መሆን ነበረበት። እዚህ በ5ኛው ምዕራፍ ውስጥ ያለው እርሱ ነበር—በ 5ኛው ምዕራፍ። እንዲህ አለ፦

> **በሰማይም ቢሆን፡ በምድርም ላይ ቢሆን፡ ከምድርም በታች ቢሆን፡ መጽሐፉን ሊዘረጋ፡ ወይም ሊመለከተው ማንም አልተቻለውም።**
>
> መጽሐፉን **ሊዘረጋ፡ የሚገባው ማንም ስላልተገኘ እጅግ አለቀስሁ** ወይም **ሊያነበው**—ወይም **መጽሐፉን ሊያነበው፡ ሊመለከተውም።**

**ከሽማግሌዎቹም አንዱ** እንዲህ አለኝ፡ **አታልቅስ፡ እነሆ፡ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ፡ እርሱም የዳዊት ሥር፡ መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ፡ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነሥቶአል** አለኝ።

እሱ ነው፡ አሁን የምንመለከተው እርሱን ነው።

148 ሩት... እና ናኦሚ፡ ቦዔዝም እንዴት ያሉ... ተምሣሌት መሆናቸውን ልብ በሉ። ኑኃሚን በረሃቡ ዘመን እንዴት ከቤተ ክርስቲያንን እንደ ወጣች፡ ከአገር እንደ ወጣች፡ በዚያ ለመኖርና በዚያ ለመቀመጥ ወደ ሞዓባውያን ምድር ገባች። በዚያም የነበራትን ሁሉ አጣች። እርሰዋም በሄደች ጊዜ፡ ባሏ፡ አቤሜሌክ፡ በዚያ ሳሉ ሞተ፡ ስለዚህም ርስቱን ለማንም እንዲወድቅ አደረገ። ከዚያም ሰንመለሰ... ተመልሳ በመጣች ጊዜ፡ መልከ መልካም የሆነችውን ሞዓባዊት መበለት ከእርሰዋ ጋር ይዛ መጣች። የክርስቶስ ተምሣሌት የነበረው ቦዔዝም፡ ይህችን መበለት ባየ ጊዜ፡ ወደቀላት። ወደዳትም። ስለዚህ፡ መቤዠት ነበረበት፡ ሚስት እንድትሆን ሊያደርጋት የሚችለው ብቸኛው መንገድ፡ ወንድሙ አቤሜሌክ ያጣውን፡ በመቤዠት ነበር።

149 እና ከሱ ይልቅ ቅርብ ዘመድ የሚሆን ሌላ ሰው ስለነበረ፡ ሌላኛውን ወንድም ጠየቀው፡ እርሱም አልችልም አለ። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ፍጹም ምሳሌ ለማድረግ ወረደ። ወደ ደጅ ሄዶ ጫማውን ከእግሩ አወጣና፡ እንዲህ አለ፡ "ኑኃሚንና ያላትን ሁሉ እንደ ተቤዠሁ ዛሬ የታወቀ ይሁን። ያላትን በሙሉ፡ የአቤሜለክ (የወንድሜ) የሆነው የጠፋበትም በሙሉ፡ አሁን ቅርብ ዋርሣ እኔ ነኝ፡ ሊበዠው የምችለው እኔ ነኝና ስለዚህም የራሴ ለማድረግ መጥቻለሁ። ትክክለኛ ምክንያትን ማሳየት የሚችል፡ ወይም ከእኔ በላይ ቅርብ የሆነ ሰው እዚህ ካለ፡ አሁን ይታወቅ።" እና ሁሉም አፋቸውን አልከፈቱም። ስለዚህም ጫማውን መትቶ ለምስክርነት ወረወረው፡ "የወንድማችን አቤሜሌክ፡ የነበረውን ሁሉ፡ ተቤዥቼዋለሁ።" ለምን? ዋርሳ ነበር። የዋርሣ ቤዛ እርሱ ነበር። ኦህ፡ እንዴት ድንቅ ነው! በጣም የሚያምር ታሪክ ነው።

150 ያኔ፡ በዚያን ጊዜ ሁሉ መካከል፡ ነገሮች እንዴት እንደሚሆኑ ለማወቅ እርፋ ትጠባበቅ ነበር። ከዚያም ተመልሶ መጣ፡ አንድም ተቃዋሚ አልገጠመውም። ተመልሶ መጣና ኑአሚንን ወሰዳት... ቆንጆይቱን ሞአባዊት፡ ሩትን ወሰዳት፡ ተጋብተውም በዚህ ርስት ላይ ኖሩ። እንዴት ያለ ድንቅ ታሪክ ነው!

151 የሩት ሦስት ደረጃዎች አሉ። ሩት—ሩት፡ **ወሰነች**፥ ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ (ልክ እንደ ቤተክርስቲያን) ውሳኔ ለማድረግ፡ ወይም ላለማድረግ ወሰነች። ሩት፡ ቃርሚያን ለመቃረም ስትወጣ፥ **አገለገለች**። ሩት፡ **አረፈች**፥ አሁን ሩት እያደረገች ያለችው ይህንን ነው (ቤት ክርስቲያን)። አሁን ሩት፡ **ትሸለማለች**፥ አሁን ያ ነው፡ ወይም፡ ቀጣዩ ነገር የሚሆነው (የቤተክርስቲያን ሽልማት ነው)።

152 አሁን፡ አንችልም... ጊዜም የለኝም፡ እናንተም የጥምቀት ስነ ስርዓት አለባችሁ አሰራ አንድ ከሩብ ሆኗል። ጌታ ቢፈቅድ ግን፡ ይህን በሚቀጥለው እሁድ ወይም ሌላ እሁድ ወደፊት እንማረዋለን። እናም እነዚህን ሰባት ቀንዶች እና ሰባት ዓይኖች፡ እና በትክክል ሰባቱን ማኅተሞች ለማሳየት፡ ይህንን እዚህ

መጻፍ እፈልጋለሁ፡ ሰባቱ አገልግሎቶች፡ ሰባት የቤተ ክርስቲያን መላእክት፡ ሰባት ከዋክብት፡ ሰ-.... ኦህ፡ ጥቂቶቹ...

153 ይኸኛውም እዚህ ጋር ደግሞ ነገሮች ሁሉ ያስተሳስራል። አዎን፡ ጌታዬ። "ብቁ ሊሆን ተገባው፡" ስለዚህ ኢየሱስ ብቁ ነው። በእርሱ መምጫ ግዜ የቤዛነት በረከቶች ሙሉ በሙሉ እናጣጥማለን። የዋሆች ምድርን ይወርሳሉና። ወንዶችና ሴቶች፥ የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች ይመለሳሉ። ያን ጊዜ ሙሉው የሚሊኒየም ማወዛወዝ ይጀምራል። እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው!

154 ብርቱው መልአክም በታላቅ ድምፅ፡ አወጀ፡ "ብቁ የሆነው ማን ነው? ይህን ማድረግ የሚችለው ማን ነው? "

155 ከሽማግሌዎቹም አንዱ "አታልቅስ፡ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሣ፡ እርሱ ድል ነስቷል እና ብቁ ነው፡" አለ።

156 "መጽሐፉንም አንሥቶ መጽሐፉን ከፈተ ማኅተሞቹንም ፈታ።" ምን እንደደረሰባቸው ተናግሮ አያውቅም ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል የተከፈቱትን ሰባት ማኅተሞች ሲነካቸው፡ የሆነውን ተመልከቱ። ይህ አሁን የገባንበት በሰባት-ማህተም በታተመው መጽሐፍ ውስጥ፡ የእግዚአብሔርን የቤዛነት በረከቶች ሁሉ ምስጢር ይዟል። አስታውሱ፡ በጉ እርሱ ነው፡ መቤዠት የሚችል ብቸኛው እርሱ ነው። እና፡ በመጽሐፉ ጀርባ የታተመ እንጂ፡ በውስጡ የተጻፈ እንዳልነበረ፡ ይህን አስታውሱ። ከጀርባው በኩል የታተመ ነው፡ ከውስጥ አልተጻፈም ነበር። መጽሐፉን መክፈት እንኳን የቻለው ወይም መጽሐፉን ሊገልጥ ወይም ማኅተሞቹን ሊገልጥ የሚችለው፡ እርሱ ብቻ ነው።

157 ስለዚህ ይህ አንድ ነገር ነው፡ እዚህ ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ፡ ስለ ምንነቱ ሊጨቃጨቁበት ይችላሉ፡ በመለኮት ትርጉም የሚተረጉመው ግን እርሱ ነው። በዚህ በጀርባው በኩል ይህን ማድረግ የሚችል ማንም የለም። የእርሱ እና የሱ ብቻ ነው፡ እና እነዚያን ሰባት ምስጢራት የሚገልጥ እርሱ ነው። ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደተቤዠች ቤዛዋስ ምን እንደሚሆን በሙሉ፡ እያንዳንዷ ጥቃቅን ነገር በቤዛነት ውስጥ እንዴት እንዳለች ተመልከቱ።

158 ኸረ፡ በፍጹም ልባችን ብቻ እነውደደው፡ የምንችለውን ሁሉ እናድርግለት።

159 አንድ ጸሐፊ አንዲት ታሪክ እየጻፈ ነበር። (ጉባኤውን ከመዝጋቴ ወይም ወደ ወንድም ኔቪል ከመመለሴ በፊት።) ራእይን ተባርካችሁበታል? ኦህ፡ እኔ ደስ ብሎኛል። ዛሬ ጥዋት ሶስት ቁጥሮችን ብቻ አይተናል፡ ደግመንም እናየዋለን። ልብ በሉ። እኛ...

160 አንድ ጸሐፊ እግዚአብሔርን ለማግኘት እየሞከረች ስለነበረች አንዲት ወጣት ልጅ መጽሐፍ እየጻፈ ነበር።

161 ብዙ ጊዜ እግዚአብሔርን እያደንን እግዚአብሔርን ስንፈልግ፡ እግዚአብሔር ግን በሁሉም ቦታ የሚገኝ ከሆነ እናንተም... ትልቁን ነገሩን... ማለት፡ ታላቁን ዛፉኑን በዚህ በአካባቢው ላይ ቢተክለው ኖሮ፡ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር ያምን ነበር። እግዚአብሔር በዚህ በአንድ ትልቅ ዛፍን ላይ ቢቀመጥ፡ ለምሣሌ፡ "በዚህች ከተማ ተቀምጧል እና ይህ እሱ ነው። ይህ አምላክ ነው እናንተም ወደ እርሱ ትሄዳላችሁ። እርሱም" [ወንድም ብራንሃም

ጣቶቹን አቃጨለ—አርታዒ።] “**እንደዚያ** ጧ ቢያደርግ፡” ታዲያስ፡ ሁሉም ያመኑት ነበር። ያን ጊዜ እምነት ከንቱ በሆነ ነበር። አያችሁ፡ እንዲህ ይሆን ነበር፡ እምነት ብሎ ነገር አይኖረንም ነበር። ያ በሚሊኒየም ውስጥ ይሆናል፡ አሁን ግን እየጠራ እና ማን ምን እንደሆነ እየመረመረ ነው... ሚስጥራዊ እና ጨለማ ይመስላል፡ እና፡ እንዴት እንደምታደርጉት አታውቁም። በእምነት ግን እናምናለን! እናምናለን። ይህ የሆነበት ምክንያቱ ይህ ነው። ይህን ተረድተሃል፡ ወንድም ኤልመር? አየህ? ያ...

162 አሁን፡ እግዚአብሔር በዙፋን ላይ ከተቀመጠ። እና እንዲህ ቢል፡ “ይኸው፡ እሱ እዚህ ነው... እዚህ አለ... እግዚአብሔር በዚህ አለ። በዚህና በዚያ ቦታ ይኖራል፡ ወደዚያም እንሄዳለን።” እና እንዲህ እንለዋለን፡ “ውድ ጌታዬ፡ እግዚአብሄር ሆይ፡ እርሶ ይህን ያደርጉልኛልን? ”

“አዎን፡ አድርግልሃለሁ።” “ፐስሰት!” ወዲያው ነገሩ ይሆናል፡ አያችሁ። “ታዲያስ፡ ይኸው እንግዲህ፡ እግዚአብሔር ነዋ። አያችሁት? ማይ፡ አየነው’ኮ።” በዚህም ምክንያት እምነት... ምንም አይጠቅምም። ልክ ከሆናችሁ እምነት ለምንም አያስፈልግም።

163 በዚህ ዓለም ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው ክርስቲያን ቢሆንስ? ሁሉም ሰው—በመንፈስ-የተሞላ ክርስቲያን ቢሆን ኖሮስ? ከእንግዲህ፡ እምነት አያስፈልገንም ነበር፡ እምነት በጭራሽ ባላስፈለገን ነበር። እምነት ደግሞ—የዳንንበት ዋናው ነገር፡ እምነት ነው። ስለዚህ እኛ እምነትን መለማመድ እንድንችል፡ በዚያ ዙርያ አለመስማማት የሚሆነው ለዚህ ነው። አሁንስ ተረድታችሁታልን? ሌላኛውን ገጽታ ደሞ ማየት አለባችሁ። አያችሁ? እውነተኛ ሴት ጎልታ ለመታየት ክፉ ሴት መኖር ነበረባት። አያችሁ? እውነትን ትክክል ለማድረግ እና ጎልቶ እንዲታይ ለማድረግ ውሸት መኖር ነበረበት። ሁሉም ነገር እውነት ቢሆን ኖሮ፡ ተራ ይሆን ነበር፡ አያችሁ። አያችሁ? ግን፡ እዩት፡ እምነት እና እውነት ወዘተ እንዲህ ሲሆን፡ ንጉሣዊ ሆኗል፡ እውነታ ይሆናል። አሁን፡ ይኸው እንግዲህ።

164 ስለዚህ፡ አንበሰ እና ጎፈር ሊኖረን የግድ ነው። አካሄዱ ያ ነው። ደስ እንዲላችሁ መልካም ቀናት ማሳለፍ አለባችሁ... ወይም መልካሙን ነገር ለማጣጣም ክፉ ቀናት ሊኖራችሁ ይገባል። መልካም ጤንነት ለማጣጣም በሽታ ቢጤ ይነካካችኋል። አያችሁ? በተራራው ጫፎች ለመደሰት ሸለቆዎችዎ ሊኖሩ ይገባል። ስለዚህ ከእነዚህ ቀናት በአንደኛው እነሆ ነገር ሁሉ ተራራ ጫፍ ይሆናል፡ ሁሉም ጤና ይሆናል፡ ሁሉም እግዚአብሔር ይሆናል፡ ሁሉም ደስታ ይሆናል፡ ብቻ... ማለቂያ—የሌላቸው ደስታዎች ይኖራሉ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ግን፡ አያችሁ፡ አንበስ እና ጎፈር ሊኖረን ይገባል።

165 አሁን፡ ይሄ የገባችሁ ሁላችሁ “አሜን፡” በሉ። [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።]

166 እና ይህች ልጅ በሄደችበት ሁሉ እግዚአብሔርን እየፈለገች መሆኗን ለሁሉም ትናገር ነበር። **ወደዚህ** ቤተክርስትያን እና **ወደዚያ** ቤተክርስትያን፡ ወደ ሌላም ትሄዳለች፡ ልታገኘው ግን አልቻለችም። እና በአንድ ወቅት እንዲህ ገጠማት፡ በመንገድ ላይ ሳለች፡ በመንገዱ የሚያልፍ ሽማግሌ ሰው ነበረ፡ ምስኪን ሰው ነበር፡ እና በጀርባው ላይ አለ የተባለው ካቴድራል ሁሉ አዝሎ

ነበር። በመንገድም እየሄደ ነበር። እርሰዋም፡ “ኡህ፡ መልካም ሰው ሆይ!” እንዲህ አለች፡ “ምስኪን፡ እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው፡” “ነገሩን ሁሉ በጀርባህ ላይ—ተ—ተሸክመሃል፡” አለችው፡ “ይህ፡ ያደቅሃል፡” አለችው።

እርሱም አላት፡ “አይ አያደቀኝም፡” “ይህ የታንበጸበት ዓለት እኔ ነኝ፡” አላት። እርሱ ነበር።

እንጸልይ፦

167 የዘመናት አለት ሆይ፡ በዓለት ላይ እያረፍን መሆናችንን፡ እኛም በካቴድራሉ ውስጥ መቀመጣችን በማወቃችን በጣም ደስ ይለናል። ኦህ፡ ዓለቱም፡ “ከወረቀት የሚበልጥ አይደለም፡” አለ። ዓለቱ በፍጥነት አብሮ መሄድ ሲጀምር፡ ከውስጥ የነበሩ ቃጭሎች ድምጽ ማውጣት ጀመሩ። የጥንት አምባ ሆይ፡ አቤቱ በምሕረት ውስጥ ሸሸገን። ልባችንን በሚያስደስት መንገድ እና በሕይወት ምንጭ ዳር ምራን በመንገዱም ሁሉ ላይ ላንተ ምስጋና ይሁን።

168 በቃሉ ውስጥ በዚህ በመንፈስ ቅዱስ ማለዳ ሰለጎበኘኸን እናመሰግንሃለን፡ በፊታችን ቀርቦ ቃሉን እውን አርጎልናልና። ጉድለታችንን ይቅር በለን እና ያደረግነውን ወይም ስህተት የሆነውን የተናገርነውን ሁሉ፡ ይቅር በለን። የተሻሉ ክርስቲያኖች እንሆን ዘንድ እርዳን፡ እግዚአብሔር አባት ሆይ። ምህረትህ እንዲያድርብን እንጸልያለን።

169 ጌታ ሆይ፡ ፈቃድህ ከሆነ፡ በቅርቡ እንደገና እንድንመለስ፡ እና እነዚህን ምዕራፎችን ሰባት ማህተሞችን አንሰተን እ—እንድንጨርስ እጠይቅሃለሁ። ጌታ ሆይ፡ አንተ ይህን እንዲሆን—የምታደርግልንን—ጊዜ፡ እነሆ—በጉጉት እንጠብቃለን። እናም፡ አባት ሆይ፡ በዚህ በቤተ ክርቲያናችን ውስጥ ይህን እንድታደርግልን እንጸልያለን፡ ይህም እነዚህን የእግዚአብሔርን ታላላቅ ነገሮች እናስተውል ዘንድ ነው። ጌታ ሆይ፡ ስለተገባን ሳይሆን፡ የተራበ ልባችን ይህን ስለሚናፍቅ ነው። እንድትፈቅድልንም እንጸልያለን።

170 ጌታ ሆይ፡ በእግዚአብሔር ስለ-ተላከው ታማኝ ፓስተር፡ ስለ ወንድማችን ኔቪል እንጸልያለን። እንድትረዳው እና እንድትባርከው እንጸልያለን፡ እንዲሁም መልካሟ ሚስቱ፡ ውብ የሆነች ነገር፡ እና ልጆቹም ባርካቸው።

171 ለባለአደራዎች እና ለዲያቆናት ወደዚህች ቤተ ክርስቲያን ለመጡት ሁሉ እንጸልያለን። ለኛ ብቻ ሳይሆን፡ ለሌሎች እና ስምህን ለሚጠሩ ሁሉም እንዲሁ። በመላ አገሪቱ ላሉ ጓደኞቼ እጸልያለሁ፡ በትንሿ ትንፋሽ ማሳሰቢያ ብቻ እዚህ ተገኝቷልና። አባት ሆይ፡ ሰ—ሰለዚህ ነገር አመሰግንሃለሁ።

172 ኢየሱስ የሚመጣበትን እና ሁላችንም የምንሰበሰብበትን ቀን እንድታፈጥን እጸልያለሁ ቀንና ሌሊት በሌለበት፡ ወይም ጊዜ በሌለበት፡ ወደ ዘላለም ተዋህደን ለዘላለም አብረን ወደምንሆንበት እንገባለን። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ።

173 እና ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ጥዋት አንተን እንደ ግል አዳኛቸው ያላወቁህ፡ አንዳንዶች ካሉ፡ በሰባት-ምስጢራዊ ማሕተም የታተመውን መጽሀፍ በእጁ የያዘውን በግ ጋር ይወግኑ። እግዚአብሔር ሆይ፡ እኛም ከእርሱ ጋር የሚወግኑ እንሁን ወደፊት እነዛ ማኅተሞች ተከፍተው ሰናይ ያን ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረንን ነገር መረዳት እንችላለን። በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን።

አንገታችንን ደፍተን ሳለን፥

174 ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ “በጸሎትህ፡ አስበኝ፡ የሚል ሰው ይኖር ይሆን፡ በጸሎት መታሰብ እፈልጋለሁ የሚል ካለ”? እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔርም ይባርክሽ፡ አንተም፡ አንቺም። አዎን። እግዚአብሔር መልካም ይሁንላችሁ። አዎን። ምናልባት ሁለት ደርዘን፡ ወይም ከዚያ በላይ እጆች፡ ተነስተዋል።

175 ጌታ ሆይ፡ እጆቻቸውን እይ፡ መሻታቸውን አንተ ታውቃለህ። በልባቸው ውስጥ ያለውን ታውቃለህ፡ እኔ አላውቅም። ጌታ ሆይ፡ ቸርነትህንና ምሕረትህን፡ እንድትገልጥላቸው እጸልያለሁ። ስለ ሁሉም ነገር ይቅር በላቸው። በሽታ ከሆነ፡ ጌታ ሆይ፡ ሰውነታቸውን ፈውሰው አድናቸውም። አባት ሆይ፡ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በጉባኤ ላይ እያለ፡ አሁን በጉባኤው ላይ ይህ ይሁን። ታላቁ የሰማይ አምላክ ሁሉንም ሰው በመለኮታዊ ፊት እንዲባርክ እንዲሁ ይቀባን፡ ዛሬ ጠዋት ከዚህ ስንሄድ፡ እንዲህ እስብለን፡ “ልባችን በውስጣችን ይነድብን አልነበረምን? ” ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ።

176 አሁን፡ ዝያለሁ ደክሞኛል፡ ድምጼም ሰልሏል፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ እንድታበረታኝ፡ ስለ ራሴ—እጸልያለሁ። ትረዳኛለህ? ታበረታኛለህ? በዚያ ውስጥ ያለውን ቁስልን አክም፡ ጌታ ሆይ። እባክህ ትወዳለህን? የእግዚአብሔር ቅዱስ ዘይት ወደዚያ፡ እና ወደ ሌላ ቁስሎች ሁሉ ይንቀሳቀስ፡ ጌታ ሆይ፡ በሁሉም ቦታ ለሁሉም ሰው ይሁን። ጌታ ሆይ፡ ለክብርህ፡ እና ለታላቅነትህ መኖር እንፈልጋለን። ይሁንልን። የታመሙትን እና የተጎዱትን ሁሉ ፈውስ። ጌታ ሆይ፡ ክብሩንም—ለአንተ ውሰድ፡ እስከምንሄድ ድረስ ብዙ እንደማይቆይ ተገንዝበናል… ከእንግዲህ እንዲህ አይነቶች ጉባኤዎች አይኖሩንም፥ ሁሉም ይጠፋሉ፡ ሁሉም ያልፋሉ።

177 አሁን፡ አባት ሆይ፡ አሁን፡ ባርከን፡ ሁሉንም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን።

178 በተጨማሪም፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ማለዳ በጌታ በኢየሱስ ስም ሊጠመቁ ያሉትን እንድታሰባቸው እንጠይቅሃለን፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ታላቅ ክብርና ምስጋናን፡ ትሰጣቸው ዘንድ እለምንሃለን። ይሁንልን፡ አባት ሆይ። አሁን ነገሩን ሁሉ ለአንተ ሰጠን።

179 እናም፡ አባት ሆይ፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ፡ እነሆ እራሴንም አማጽናለሁ። ጌታ ሆይ፡ አትርሳኝ፡ አሁኑኑ እርዳኝ። በኢየሱስ ስም ጸለይኩ። አሜን።

61-0611 ራእይ፡ ምዕራፍ አምስት ክፍል I
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤሰ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org